አላህን ማወቅ

ዝግጅት፦ ዶክተር ሷሊህ አል-ሷሊህ رَحِمَهُ ٱللَّهُ

15-8-1427 ሒጅራ

አጠር ያሉ ማብራሪያዎች
በሳዳት አማል አቡ መርየም

Sadat.kemal Tewhidfirst Sadatkemalabumeryem Ehiotewhid

ማውጫ

አላህ ማን ነው?..... 1

ጌታችሁ አላህ ነው። እሱን ብቻ እንጂ ከእሱ ውጭ ሌላን አትገዙ (አታምልኩ).....16

አላህ ስለመኖሩ ማስረጃዎች.....29

አጠቃላይ መልእክት.....47

ከኛ በፊት ለነበሩ ህዝቦች የተላለፈ መልእክት.....48

የመጨረሻው መልክተኛ (ﷺ).....56

የሕይወት አላማ.....58

ማስረጃዎችን ማቅረብ (ሁጃ).....60

ለሚወስዱት ውሳኔ የመወሰን ሃላፊነት.....61

ውጤቱ.....63

ስለዚህ (እሺ) አቋምህ የት ላይ ነው? 65

እጅግ በጣም ሩህሩህና አዛኝ በሆነው አላህ ስም እጀምራለሁ

አላህ ማን ነው?

*አላህ ከምንም በፊት የነበረው የብቸኛው ፈጣሪያችን ስም ነው። **ፈጣሪያችን አላህን በወዲያኛው አለም እንጂ በዚህ አለም በፍፁም ማየት አንችልም**። **አማኞች አማኝ ከተሰኙባቸው ዋና ዋና ነጥቦች መካከል እርሱን በአካል ሳይመለከቱ በእርሱ ማመናቸው ነው**።*

***የአላህን ማንነት ከምናውቅባቸው ብቸኛ ምንጮቻችን መካከል አላህ በነብያቶች ላይ ያወረዳቸው መፅሀፍት ናቸው**። ከእነሱ መካከል በመጨረሻው መልክተኛ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ላይ ያወረደው ቁርአን ነው። **ቁርአን የአላህ ቃል ነው**። **ስለ አላህ ከአላህ በላይ ሊነግረን የሚችል አንድም አካል የለም**። እኛ ፍጡሮቹ ስለ እሱ ጠንቅቀን ማወቃችን ለእኛ በጣም ወሳኝ ነው። ምክንያቱም እሱን በሚገባ ሳናውቅ የተፈጠርንለትን አላማ (አምልኮ) ማሳካት አንችልምና። አላህ ስለ እሱ ማንነት በስሞቹና በመገለጫዎቹ በተከበረው ቁርአኑ በደንብ አብራርቶ ነግሮናል። ከዚህ ቢታች የተዘረዘሩ ቁርአናዊ አንቀፆች የአላህን ማንነት ይበልጥ ግልፅ ያደርጉልናል።*

﴿ قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۝١ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۝٢ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ۝٣ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ۝٤ ﴾

الإخلاص: ١ - ٤

በል[1] **"እርሱ አላህ <u>አንድ ነው</u>። አላህ <u>(የሁሉ) መጠጊያ ነው</u>። <u>አልወለደም</u>፤ <u>አልተወለደምም</u>። <u>ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም</u>።"**[2] [አል ኢኽላስ 1-4]

---

[1] አላህ ነብዩን (ﷺ) በል ሲላቸው እሳቸው አድራሽ መልክተኛ ብቻ መሆናቸውን እና **<u>ቁርዓን የአላህ ቃል ለመሆኑ ታላቅ ማስረጃ ነው</u>**።

[2] ይህች ምእራፍ ሱረቱል ኢኽላስ በመባል ትታወቃለች። የቁርዓን 1/3ኛ የምትስተካከል አንቀፅ ነች። ምዕራፏ ስለ አላህ ማንነት የምትዳስስ፣ ለእርሱ የሚገቡትን የተሟሉ ስሞች እና ባህሪያት ስታፀድቅ፣ ጎዶሎነትን፣ ጉድለትን እና ነውርን ደግሞ ከአላህ ላይ ውድቅ ታደርጋለች። ይህች ምዕራፍ የወረደችበት ሰበብ የመካ ካሃዲያን ነብዩ (ﷺ) ዘንድ መጡና **<u>"የጌታህን የዘር ሀረግ ንገረን?"</u>** በማለት ጠየቋቸው። ከዚያም የአላህን ማንነት በደንብ የምታስተዋውቀው ይህች ምዕራፍ ወረደች።

ይህች ሱራ (ምዕራፍ) ስለ አላህ ባህሪ በደንብ ታብራራለች። አላህ አንድ የሆነ፣ ለእርሱ ቢጤም፣ አጋዥም፣ አጋርም፣ አምሳያም የሌለው፣ የፍጡራኑ ሁሉ መጠጊያ፣ ብቸኛ መሆኑን ታስረዳለች። ***<u>የሁዳዎች ኡዘይርን ነሷራዎች ደግሞ ነብዩላህ ኢሳን (ኣለይሂ ሰላም) የአላህ ልጆች ናቸው ብለዋል</u>።*** ***<u>የመካ ሙሽሪኮች (ኣጋሪያን) ደግሞ መላእክት የአላህ ሴት ልጆች ናቸው በማለት ቀጥፈዋል</u>።*** ***<u>እውነታው ግን በዚህ ተቃራኒ ነው</u>።*** ***<u>ፈጣሪያችን አላህ ወንድ ልጆችም፣ ሴት ልጆችም፣ ሚስትም የሌለው መሆኑ ነው</u>።*** *አላህ ይህን አባባል ትክክል እንዳልሆነ እና* ***<u>የማንም አባት፣ የማንም ልጅ አለመሆኑን እና ለእርሱም ልጅ እንደሌለው መልሰ ሲሰጥ “አልወለደም፣ አልተወለደም”</u>*** *ብሎ በግልፅ ነግሮናል። ይህ (ለአላህ ልጅ አለው የሚለው አባባል እና እምነት) ከአላህ የሙሉነት ባህሪ ጋር በፍፁም የሚሄድ አይደለም። ጌታችን አላህ ከጉድለት ሁሉ የጠራ ነው።*

﴿ إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ يَطْلُبُهُۥ حَثِيثًا

وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتٍۭ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٥٤﴾ ﴾ الأعراف: ٥٤

“ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን <u>በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው</u>። <u>ከዚያም ከዐርሹ በላይ ከፍ አለ</u>[3]። <u>(አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል</u>። <u>ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)</u>። <u>ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው</u>። <u>የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ</u>።

[አል-አዕራፍ 54]

በዚህ አንቀፅ ***<u>ጌታችን አላህ ከሰባት ሰማያት እና ከአርሹ በላይ ከፍ ያለ ነው</u>።*** ***<u>ብቸኛው ፈጣሪ፣ አዛዥ እና ተመላኪ መሆኑን ተናገረ</u>።*** ***<u>ፍጡራን የፈለገውን ያህል ደረጃቸው ትልቅ ቢሆን (ለምሳሌ መለኣኩ ጂብሪል፣ ነብዩ ሙሐመድ ﷺ) ብቸኛውን ፈጣሪ አላህን አምላኪዎች እንጂ ተመላኪዎች አይደሉም</u>።*** *አላህ የሚከተሉትን ቁርኣናዊ አንቀፆች አውርዷል*

[3] ***<u>“ኢስተዋ”</u>*** የሚለው ቃል ትርጉም ***<u>ከፍ አለ</u>***፣ ***<u>ከበላይ ሆነ</u>*** የሚል ነው። ኢማም አል- ቡኻሪ (አላህ ይዘንላቸው) ከአቡል አልያ ይዘው በሶሂህ ኪታባቸው ላይ ዘግበውታል።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ ٱلْكِتَٰبَ بِٱلْحَقِّ وَٱلْمِيزَانَ ۗ وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّ ٱلسَّاعَةَ قَرِيبٌ ﴿١٧﴾ ﴾ الشورى: ١٧

አላህ ያ መጽሐፉን[4] በእውነት ያወረደ ነው። ሚዛንንም (እንደዚሁ)። ሰዓቲቱ ምንአልባት ቅርብ መኾንዋን ምን ያሳውቅሃል? [አል ሹራ 17]

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُوا۟ رَبَّكُمُ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَٰحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَآءً ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ٱلَّذِى تَسَآءَلُونَ بِهِۦ وَٱلْأَرْحَامَ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا ﴿١﴾ ﴾ النساء: ١

እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም (ከአዳም እና ሄዋን) ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን (አላህ) ፍሩ።ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ። አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና። [አል-ኒሳዕ 1]

አላህ በሚከተሉት ደረጃዎች እና እርከኖች የሰው ልጆችን ፈጥሯል

- *የሰው ልጆችን አባት አደም (አለይሂ ሰላም) ከአፈር ፈጠረ፣*
- *የሰው ልጆችን እናት ሃዋን ከአደም (አለይሂ ሰላም) ከጎን አጥንት ፈጠረ፣*
- *የተቀሩትን የሰው ልጆች ከወንድ እና ከሴት ፈጠረ፣*
- *ነብዩላህ ኢሳን (አለይሂ ሰላም) ያለ አባት ከእናት ብቻ በመፍጠር የተሟላ ችሎታውን አስመሰከረ።*

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ማለትም አደም እስከ ባለቤታቸው ሃዋ፤ ኢሳ እስከ እናታቸው መርየም የሰው ልጆች ሲሆኑ አላህን ለማምለክ የተፈጠሩ እንጂ የሚመለኩ አይደሉም።

[4] አላህ መለኮታዊ መፅሃፍትን ለነብያቱ ያወርዳል። ነብያቱም ለሰው ልጆች የአላህን መልእክት ሊያብራሩ እና በተግባር አምልኮዎች እንዴት እንደሚፈፀሙ ሊያሳዩ ከእርሱ ይላካሉ።

﴿ إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ ۖ يُدَبِّرُ ٱلْأَمْرَ ۖ مَا مِن شَفِيعٍ إِلَّا مِنۢ بَعْدِ إِذْنِهِۦ ۚ

ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ فَٱعْبُدُوهُ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٣﴾ ﴾ ዩኑስ: ፫

ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው። ከዚያም ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብር ሲኾን ከዐርሹ በላይ ሆነ። ከእርሱ ፈቃድ በኋላ ቢኾን እንጂ አንድም አማላጅ የለም። እነሆ! አላህ ጌታችሁ ነውና ተገዙት (በብቸኝነት አምልኩት)፤ አትገሰጹምን!!! [ዩኑስ 3]

*በዚህ አንቀፅ አላህ **ብቸኛው ፈጣሪ እና አስተናባሪ እርሱ ብቻ በመሆኑ እርሱን ብቻ እንድናመልከው አዟል።** ከዚህም በተጨማሪ የሰው ልጆች ከአላህ ውጪ ያሉ አካላትን የሚያመልኩት ምልጃን ፍለጋ በመሆኑ **አማላጅ የሚሆነው ማንኛውም አካል ከአላህ ዘንድ የማማለድ ፍቃድ ማግኘት እንዳለበት፣ ምልጃ የሚጠየቅለት አካል ደግሞ የአላህን ውዴታ ማግኘት እንዳለበት አረጋገጠ።***

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى رَفَعَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ بِغَيْرِ عَمَدٍ تَرَوْنَهَا ۖ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ ۖ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ ۖ كُلٌّ يَجْرِى لِأَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ يُدَبِّرُ ٱلْأَمْرَ

يُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ لَعَلَّكُم بِلِقَآءِ رَبِّكُمْ تُوقِنُونَ ﴿٢﴾ ﴾ الرعد: ፪

አላህ ያ ሰማያትን የምታዩዋት አዕማድ (ምሶሶ) ሳትኖር ያነሳት (ከፍ አድርጎ ከበላይ ያደረጋት) ከዚያም ከዐርሹ በላይ ከፍ ያለ ፀሐይንና ጨረቃንም ያገራ ነው። ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ። ነገሩን ሁሉ ያስተናብራል። በጌታችሁ መገናኘት ታረጋግጡ ዘንድ ተዓምራቶችን ይዘረዝራል። [አል-ረዕድ 2]

*ይህ አንቀፅ ደግሞ **ሰማይን ያለ ሙሶሶ በማቆሙ የአፈጣጣር ችሎታው ድንቅ መሆኑን የገለፀበት ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ ብቸኛ አስተናባሪው እርሱ እንደሆነ፣** ከገደለም በኋላ እንደሚቀሰቅሰን **ከዛም ለሂሳብ እንደሚያቀርበን አሰረግጦ የተናገረበት አንቀፅ ነው።***

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزْقًا لَّكُمْ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلْفُلْكَ لِتَجْرِىَ فِى ٱلْبَحْرِ بِأَمْرِهِۦ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلْأَنْهَٰرَ ﴿٣٢﴾ ﴾ إبراهيم: ٣٢

<u>አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ከሰማይም ውሃን ያወረደ በእርሱም ከፍሬዎች ሲሳይን ለእናንተ ያወጣ መርከቦችንም በፈቃዱ በባሕር ላይ ይንሻለሉ ዘንድ ለናንተ ያገራ ወንዞችንም ለናንተ ያገራ ነው።</u> [ኢብራሂም 32]

አላህ ያ <u>ብቸኛው ሲሳይ ሰጪ እርሱ መሆኑን፣ መርከቦችን በፍቃዱ ሰንት እና ሰንት የባህር መንገዶችን እንዲያቋርጡና ማድረጉን፣ ወንዞችን በማግራት ለሰው ልጆች እንዲመቹ ያደረገ መሆኑን ይገልፃል። በዚህ እና በመሰል አንቀፆች የአላህ ፀጋ በእኛ ላይ ተቆጥሮ እንደማያልቅ እንገነዘብበታለን።</u>

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِى مَدَّ ٱلْأَرْضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَٰسِىَ وَأَنْهَٰرًا ۖ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ جَعَلَ فِيهَا زَوْجَيْنِ ٱثْنَيْنِ ۖ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٣﴾ ﴾ الرعد: ٣

<u>እርሱም (አላህ) ያ ምድርን የዘረጋ በሷም ተራራዎችንና ወንዞችን ያደረገ በውስጧም ከፍሬዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ዓይነቶችን ያደረገ ነው።</u> <u>ሌሊትን በቀን ይሸፍናል</u>። በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉ። [አል-ረዕድ 3]

እዚህ አንቀፅ ላይ አላህ ለአእምሮ ባለቤቶችና ለሚያስተነትኑ ሰዎች የዋለውን ውለታ፣ የእርሱን ችሎታ እና ታዓምራት ይዘረዝርላቸዋል።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَكُمْ ثُمَّ رَزَقَكُمْ ثُمَّ يُمِيتُكُمْ ثُمَّ يُحْيِيكُمْ ۖ هَلْ مِن شُرَكَآئِكُم مَّن يَفْعَلُ مِن ذَٰلِكُم مِّن شَىْءٍ ۚ سُبْحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٤٠﴾ ﴾ الروم: ٤٠

<u>አላህ ያ የፈጠራችሁ፣ ከዚያም ሲሳይን የሰጣችሁ፣ ከዚያም የሚገድላችሁ ከዚያም ሕያው የሚያደርጋችሁ ነው</u>። ከምታጋሯቸው (ጣዖታት) ውስጥ ከዚህ ነገር አንዳችን የሚሠራ አለን? ለአላህ ጥራት ይገባው። (በእርሱ) ከሚያጋሩትም ሁሉ ላቀ። [አል-ረዕድ 40]

<u>እንደሚታወቀው አላህ ዘንድ ታላቁ በደል በእርሱ ላይ ማጋራት (ሺርክ) ነው</u>። በአላህ ላይ ማጋራት ማለት አምልኮ ለብቸኛው ፈጣሪ አንድ አምላ አላህ ብቻ ሊፈፀም ሲገባው፣ ከአላህ ውጭ ለማንኛውም ፍጡር (መላእክ፣ ነብይ፣ ደጋጎች) ቢሰጥ ሺርክ ወይንም በአላህ ላይ ማጋራት ይባላል። <u>አላህ አጋሪያን ከሚቀጥፉት ሁሉ የጠራ መሆኑን በዚሁ አንቀፅ ላይ ይጠቅሳል</u>። *የፈጠረን፣ ሲሳይን የሚለግሰን፣ የማይቀረውን ሞት የሚገድለን እናም ከሞት በኋላ ቀስቅሶ ሂሳብ የሚከፍለን፣ አንድ ፈጣሪ፣ አንድ አምላክ፣ የሆነው አላህ ነው። ለአላህ ያማሩ ሥሞች የተከበሩ መገለጫዎች (ባህሪዎች) አሉት።*

﴿ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ دَآئِبَيۡنِۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ ٣٣ ﴾ إبراهيم: ٣٣

<u>(አላህ) ፀሐይንና ጨረቃንም ዘወትር ኼያጆች ሲኾኑ ለእናንተ ያገራ ሌሊትንና ቀንንም ለእናንተ ያገራላችሁ ነው</u>። [ኢብራሂም 33]

ፀሐይን፣ ጨረቃን፣ ቀንን እና ሌሊትን ለእኛ ማግራቱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ መሆኑን ያስገነዝበናል። ***<u>አምልኮ ደግሞ የሚገባው ሁሉንም ነገር ፈጣሪ፣ አስተናባሪ እና ቻይ ለሆነው አላህ ብቻ እና ብቻ ነው</u>።***

﴿ وَءَاتَىٰكُم مِّن كُلِّ مَا سَأَلۡتُمُوهُۚ وَإِن تَعُدُّواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ لَا تُحۡصُوهَآۗ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَظَلُومٞ كَفَّارٞ ٣٤ ﴾

إبراهيم: ٣٤

<u>(አላህ) ከለመናችሁትም ሁሉ የሰጣችሁ ነው</u>። <u>የአላህንም ፀጋ ብትቆጥሩ አትዘልቋትም</u>። ሰው በጣም በደለኛ ከሓዲ ነው። [ኢብራሂም 34]

<u>አላህ ከሰሞቹ አንዱ “አል-ራህማን” (እዝነቱ ሁሉንም የሚያካትት) ማለት ነው</u>። <u>የለመኑትን መልስ የሚሰጠው እርሱ ብቻ ነው</u>። *ይህ ሆኖ ሳለ፣ የሰው ልጅ፣ ከአላህ*

ውጭ ያለን ያመልካል፣ ይጣራል፣ ይለምናል። <u>ለዚህ ነው አላህ የሰው ልጅ በጣም በደለኛ ካሃዲ ነው በማለት የተናገረው</u>።

﴿ ۞ أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ قَادِرٌ عَلَىٰٓ أَن يَخۡلُقَ مِثۡلَهُمۡ وَجَعَلَ لَهُمۡ أَجَلٗا لَّا رَيۡبَ فِيهِ فَأَبَى ٱلظَّٰلِمُونَ إِلَّا كُفُورٗا ٩٩ ﴾ الإسراء: ٩٩

<u>ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ አላህ</u> <u>ብጤያቸውን በመፍጠር ላይ ቻይ መኾኑን</u> <u>በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበትም ጊዜ</u> <u>(ለሞትም ለትንሣኤም)</u> <u>ለእነርሱ የወሰነ መኾኑን አላወቁምን</u>!!! በደለኞችም ከክህደት በቀር እምቢ አሉ። [አል ኢስራዕ 99]

አሁንም አላህ እራሱን እያሰተዋወቀን ነው። <u>ብቸኛው የሁሉ ነገር ፈጣሪ መሆኑን አሰገነዘበን</u>።

﴿ إِنَّمَآ إِلَٰهُكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ وَسِعَ كُلَّ شَيۡءٍ عِلۡمٗا ٩٨ ﴾ طه: ٩٨

<u>ጌታችሁ</u> <u>ያ ከእርሱ በቀር</u> <u>በሐቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የሌለ የኾነው</u> <u>አላህ ብቻ ነው</u>። <u>እውቀቱ ነገርን ሁሉ አዳረሰ</u>። [ጣሃ 98]

እውቀተ ሰፊ መሆኑን እና ብቸኛ አምላክ መሆኑን ከእርሱ በቀር በሃቅ የሚመለክ እንደሌለ ተናገረ።

﴿ ۞ ٱللَّهُ نُورُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ مَثَلُ نُورِهِۦ كَمِشۡكَوٰةٖ فِيهَا مِصۡبَاحٌۖ ٱلۡمِصۡبَاحُ فِي زُجَاجَةٍۖ ٱلزُّجَاجَةُ كَأَنَّهَا كَوۡكَبٞ دُرِّيّٞ يُوقَدُ مِن شَجَرَةٖ مُّبَٰرَكَةٖ زَيۡتُونَةٖ لَّا شَرۡقِيَّةٖ وَلَا غَرۡبِيَّةٖ يَكَادُ زَيۡتُهَا يُضِيٓءُ وَلَوۡ لَمۡ تَمۡسَسۡهُ نَارٞۚ نُّورٌ عَلَىٰ نُورٖۗ يَهۡدِي ٱللَّهُ لِنُورِهِۦ مَن يَشَآءُۚ وَيَضۡرِبُ ٱللَّهُ ٱلۡأَمۡثَٰلَ لِلنَّاسِۗ وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ ٣٥ ﴾النور: ٣٥

<u>አላህ የሰማያትና የምድር ብርሃን ነው</u>። የብርሃኑ ምሳሌ በውስጧ መብራት እንዳለባት (ዝግ) መስኮት፣ መብራቱ በብርጭቆ ውስጥ የኾነ፣ ብርጭቆይቱ ፍፁም ሉላዊ ኮከብ የምትመስል፣ ምሥራቃዊው ምዕራባዊም ካልኾኑች ከተባረከች የወይራ ዛፍ ዘይቷ እሳት

ባይነካውም እንኳ ሊያበራ የሚቀርብ ከኾነች (ዘይት) የሚቃጠል እንደ ሆነ (መብራት) ነው። (ይህ) በብርሃን ላይ የኾነ ብርሃን ነው። አላህ ወደ ብርሃኑ የሚሻውን ሰው ይመራል። አላህም ለሰዎች ምሳሌዎችን ያቀርባል። አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው። [አል ኑር 35]

አላህ የሰማያት እና የምድር ብርሃን እንደሆነ ገለፀ። አላህ የፈለገውን እንደሚመራ። አላህ ምሳሌዎችን እንደሚሰጥ። አላህ በነገሩ ሁሉ አዋቂ መሆኑን ነገረን።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى يُرۡسِلُ ٱلرِّيَٰحَ فَتُثِيرُ سَحَابٗا فَيَبۡسُطُهُۥ فِى ٱلسَّمَآءِ كَيۡفَ يَشَآءُ وَيَجۡعَلُهُۥ كِسَفٗا فَتَرَى ٱلۡوَدۡقَ يَخۡرُجُ مِنۡ خِلَٰلِهِۦۖ فَإِذَآ أَصَابَ بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦٓ إِذَا هُمۡ يَسۡتَبۡشِرُونَ ﴿٤٨﴾ ﴾ الروم: ٤٨

<u>አላህ ያ ንፋሶችን የሚልክ ነው</u>። ደመናንም ይቀሰቅሳሉ። በሰማይ ላይም እንደሚሻ ይዘረጋዋል። ቁርጥራጮችም ያደርገዋል። ዝናቡንም ከደመናው መካከል ሲወጣ ታያለህ። <u>በእርሱም ከባሮቹ የሚሻውን በለየ ጊዜ ወዲያውኑ እነሱ ይደሰታሉ</u>። [አል ሩም 48]

ዝናብን የሚያዘንብ እርሱ መሆኑን ነገረን። ከባርያዎቹ የእርሱ ጥበብ እና ውሳኔ ወዳስፈረደችበት ያ ዝናብም ይዘንባል። ለምሳሌ በተወሰነ ክልል ዘንቦ በሌላው የምድር ገፅ የዝናብ ጠብታ እንኳ ላይኖር ይችላል። ምክንያቱም አላህ ዝናብ እንዲደርስ የፈለገ ለእዛ የተወሰነ ክልል ብቻ በመሆኑ ነው።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن ضَعۡفٖ ثُمَّ جَعَلَ مِنۢ بَعۡدِ ضَعۡفٖ قُوَّةٗ ثُمَّ جَعَلَ مِنۢ بَعۡدِ قُوَّةٖ ضَعۡفٗا وَشَيۡبَةٗۚ يَخۡلُقُ مَا يَشَآءُۖ وَهُوَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡقَدِيرُ ﴿٥٤﴾ ﴾ الروم: ٥٤

<u>አላህ ያ ከደካማ (ፍትወት ጠብታ) የፈጠራችሁ ነው</u>። <u>ከዚያም ከደካማነት በኋላ ጎይልን አደረገ</u>። <u>ከዚያም ከብርቱነት በኋላ ደካማነትንና ሽበትን አደረገ</u>። <u>የሚሻውን ይፈጥራል</u>። <u>እርሱም ዐዋቂው ቻዩ ነው</u>። [አል ሩም 54]

<u>አላህ</u> ደካማነታችንን በተለያየ ደረጃ ካሰቀመጠ በኋላ፣ <u>የፈለገውን እንደሚፈጥርፈጣሪ፣ በእርሱም ላይ አዋቂ እና ቻይ መሆኑንም ተናገረ</u>።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ ۖ مَا لَكُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَلِىٍّ وَلَا شَفِيعٍ ۚ أَفَلَا تَتَذَكَّرُونَ ﴿٤﴾ ﴾ السجدة: ٤

<u>አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ከዚያም ከዐርሹ በላይ ከፍ አለ</u>። <u>ከእርሱ ሌላ ለእናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም፤ አትገሰጹምን?</u> [አል ሰጅዳህ 4]

አላህ ብቸኛው ረዳት እና ለአማላጆች ብቸኛው ፍቃድ ሰጪ እርሱ ብቻ መሆኑን፣ ያለማንም ረዳት ሰማያት እና ምድርን በስድስት ቀናት ከፈጠረ በኋላ ከዐርሹ በላይ ከፍ እንዳለ ተናገረ።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ لِتَسْكُنُوا۟ فِيهِ وَٱلنَّهَارَ مُبْصِرًا ۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَذُو فَضْلٍ عَلَى ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَشْكُرُونَ ﴿٦١﴾ ﴾ غافر: ٦١

<u>አላህ ያ ለእናንተ ሌሊትን በውስጡ ልታርፉበት</u> (ጨለማ) <u>ቀንንም</u> (ልትሠሩበት) <u>የሚያሳይ ያደረገላችሁ ነው</u>። <u>አላህ በሰዎች ላይ በእርግጥ የቸሮታ ባለቤት ነውና</u>። ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያመሰግኑም። [አል ጋፊር 61]

*አብዛኞቹ ባያመሰግኑም **በቀኑ ሰአት ሰራን እንዲሰሩ፣ በለሊቱ ሰአት ደግሞ እንዲርፉ ህግን ደነገገ**። ደካማውን የሰው ልጅ በሌሊቱ ከፍለ ጊዜ በመተኛት እንዲያርፍ እና በቀኑ ከፍለ ጊዜ እንዲሰራ ያደረገው ጥበበኛው አላህ ምስጋና ይገባው።*

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلْأَرْضَ قَرَارًا وَٱلسَّمَآءَ بِنَآءً وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ وَرَزَقَكُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ ۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ ۖ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٤﴾ ﴾ غافر: ٦٤

<u>አላህ ያ ምድርን መርጊያ ሰማይንም ጣሪያ ያደረገላችሁ ነው።</u> <u>የቀረጻችኁም ቅርጻችሁንም ያሳመረ</u> <u>ከጣፋጮችም ሲሳዮች የሰጣችሁ ነው።</u> <u>ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው።</u> <u>የዓለማትም ጌታ አላህ ላቀ።</u> [አል ጋፊር 64]

ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ በማድረግ ላይ ቻይ የሆነው አላህ እራሱን እንዲህ ሲል አስተዋወቀ "<u>ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው።</u> <u>የአለማትም ጌታ አላህ ላቀ።</u>" <u>ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ አለም በመባል ይጠራል</u>። ታድያ የሰው ልጅና ኢጋንንት <u>ፈጣሪያቸውን አላህ ብቻ እንጂ ማንንም ሊያመልኩ አይገባቸውም</u>።

﴿ ۞ ٱللَّهُ ٱلَّذِي سَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡبَحۡرَ لِتَجۡرِيَ ٱلۡفُلۡكُ فِيهِ بِأَمۡرِهِۦ وَلِتَبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِهِۦ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ١٢ ﴾ الجاثية: ١٢

<u>አላህ ያ ባሕርን በውስጡ ታንኳዎች በፈቃዱ እንዲንሻለሉበት</u> <u>ከችሮታውም እንድትፈልጉበት</u> <u>እንድታመሰግኑትም ለእናነተ ያገራላችሁ ነው</u>። [አል ጃሲያህ 12]

<u>ታላላቅ ባህሮች ላይ መርከቦች እንዲንቀሳቀሱ ፍቃድ መሰጠቱን እና የችሮታ ባለቤት መሆኑን ተናገረ</u>። <u>መርከቦች ከባህሩ ታላቅነት አኳያ ሲታዩ በጣም ኢምንት (ትንሽ) ናቸው</u>። ይህ ከመሆኑም ጋር <u>አዛኙ አላህ በፍቃዱ መርከቧን ያንሻልላታል (ያሰጉዛታል)</u>። እኛም አላህን አመስጋኞች እና አወዳሾች መሆን አለብን። አላህ እሱን ከሚያመሰግኑት ያድርገን።

﴿ وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ١٣ ﴾ الجاثية: ١٣

<u>ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ</u> <u>ከእርሱ (ከአላህ) ሲኾን ያገራላችሁ ነው</u>። በዚህ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ተዓምራት አልለበት። [አል ጃሲያህ 13]

በሰማያት እና በምድር ያለውን ሁሉ ለሰው ልጅ የገራ መሆኑን አላህ ተናገረ። የአላህን ታዓምራት ማስተዋል፣ ማስተንተን፣ ልብ ማለት ከእኛ ይጠበቃል።

﴿ أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَلَمۡ يَعۡيَ بِخَلۡقِهِنَّ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يُحۡۦِيَ ٱلۡمَوۡتَىٰۚ بَلَىٰٓۚ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٣٣ ﴾ الأحقاف: ٣٣

<u>ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ እነርሱንም በመፍጠሩ ያልደከመው አላህ ሙታንን ሕያው በማድረግ ላይ ቻይ መኾኑን አላስተዋሉምን? (በማስነሳት) ቻይ ነው። እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።</u> [አል አህቃፍ 33]

<u>አይሁዶች እና ነሷራዎች ፈጣሪ አለምን ፈጥሮ ካበቃ በኋላ ድካም ሰለተሰማው አረፈ ይላሉ</u> *(አላህ ከሃዲዎች ከሚሉት ሁሉ የጠራ ነው)፣* ***<u>ሙስሊሞች ግን አላህን ድካም እንደማታገኘው፣ ሁሉንም ነገር የማድረግ ችሎታ እንዳለው፣ አንድ ነገር መወሰን ከፈለገ ሁን ይለዋል ወዲያውኑ እንደሚሆን ያምናሉ።***

﴿ هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِى لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ عَٰلِمُ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ ۖ هُوَ ٱلرَّحْمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٢٢﴾ ﴾ الحشر: ٢٢

<u>እርሱ አላህ ነው፤ ያ ከእርሱ በቀር በሐቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የሌለ፣ ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የኾነ ነው። እርሱ እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ ነው።</u> [አል ሐሽር 22]

<u>የሩቅ እና የቅርቡን የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው</u>*። ከአላህ ውጪ ያሉ አካላት ጠንቋይም ይሁን ወልይ፣ መላኢካም ይሁን ረሱል የሩቅን ሚስጥር ሊያውቁ አይችሉም። ሀገራችን ላይ የሸይኽ ሁሴን ጂብሪል ትንቢት የሚባለው ክህደት ነው። ምክንያቱም የነገን የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው። በሁለተኝነት አላህ ከመልከተኞቹ ለፈለገው እና ለመረጠው ከፊል የእሩቅ እውቀትን ያሳውቃል። ከነብያችን (ﷺ) በኋላ ደግሞ ነብይ የለም። ሁሴን ጂብሪል የሚባለው ግለሰብ ሰለ ነገ ተናግሮታል የሚባለው ነገር ክህደት ነው። ነብዩ (ﷺ) "የነገን አውቃለሁ ባይ ዘንድ የሄደ የ40 ለሊት ሰላቱ ተበላሽቷል። ካመነበት በእኔ ላይ በተወረደው ኪዷል" ብለዋል። ሁሴን ጂብሪል የተባለው ግለሰብ ተናግሯል የሚሉት የጥንቆላ እና የትንቢት ስራ ስለሆነ ጌታውን ከክህደት ተቆጥቦ መገናኘት የፈለገ ሰው ከዚህ የጥንቆላ ስራ እራሱን ሊያርቅ ይገባዋል።*

﴿ هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِى لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْمَلِكُ ٱلْقُدُّوسُ ٱلسَّلَٰمُ ٱلْمُؤْمِنُ ٱلْمُهَيْمِنُ ٱلْعَزِيزُ ٱلْجَبَّارُ ٱلْمُتَكَبِّرُ ۚ

سُبْحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ الحشر: ٢٣

እርሱ አላህ ነው። ያ ከእርሱ በቀር በሐቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሡ ከጉድለት ሁሉ የጠራው፣ የሰላም ባለቤቱ፣ ጸጥታን ሰጪው፣ ባሮቹን ጠባቂው፣ አሸናፊው፣ ኃያሉ፣ ኩሩው ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ። [አል ሐሽር 23]

*በዚህ አንቀፅ **አምልኮ ለእርሱ ብቻ እንደሚገባ፣ አጋሪያን በርሱ ላይ ከሚያጋሩበት ሁሉ የጠራ መሆኑን የሙሉ ሰምቾና ባህሪያት ባለቤት የሆነው አላህ ተናገረ።***

﴿ هُوَ ٱللَّهُ ٱلۡخَٰلِقُ ٱلۡبَارِئُ ٱلۡمُصَوِّرُ لَهُ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰۚ يُسَبِّحُ لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٢٤ ﴾

الحشر: ٢٤

እርሱ አላህ ፈጣሪው (ከኢምንት) አስገኚው፣ ቅርጽን አሳማሪው ነው። ለእርሱ መልካሞች ስሞች አልሉት። በሰማያትና በምድርም ያለው ሁሉ ለእርሱ ያሞግሳል። እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው። [አል ሐሽር 24]

*በዚህ የቁርኣን አንቀፅ ደግሞ የመልካም ስሞች ባለቤት እንደሆነ እና **በሰማይም በምድርም ያለው ሁሉ እርሱን እንደሚያሞግሱ ተናገረ።***

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ وَمِنَ ٱلۡأَرۡضِ مِثۡلَهُنَّۖ يَتَنَزَّلُ ٱلۡأَمۡرُ بَيۡنَهُنَّ لِتَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ وَأَنَّ ٱللَّهَ قَدۡ أَحَاطَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عِلۡمَۢا ١٢ ﴾ الطلاق: ١٢

"አላህ ያ ሰባትን ሰማያት የፈጠረ ነው። ከምድርም መሰላቸውን (ሰባት ምድሮችን ፈጥሯል)፣ በመካከላቸው ትእዛዙ ይወርዳል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን አላህም በነገሩ ሁሉ በዕውቀት ያካበበ መኾኑን ታወቁ ዘንድ (ይህንን አሳወቃችሁ)። [አል ጠላቅ 12]

አላህ ሰባትን ሰማያት እና ምድር የፈጠረ፣ በነገሩ ሁሉ እውቀቱ ያካበበ መሆኑን እንድንገነዘብ በተከበረው ቁርኣኑ ገለፀልን።

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ٢٥٥ ﴾ البقرة: ٢٥٥

<u>አላህ ከእርሱ በቀር በሐቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የለም</u>። <u>ሕያው ራሱን ቻይ ነው</u>። <u>ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም</u>። <u>በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው</u>። <u>ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው?</u> (ከፍጡሮች) <u>በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል</u>። <u>በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)</u>። <u>ኩርስዩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ</u>። <u>ጥበቃቸውም አያቅተውም</u>። <u>እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው</u>። [አል-በቀራህ 255]

ይህች አንቀፅ ከቁርዓን አንቀፆች ሁሉ በላጪ ስትሆን [5] የአላህን በሐቅ ተመላኪነት፣ የእሱን ሙሉነት፣ በሰማይ በምድር ያለው ሁሉ የእሱ ብቻ እንደሆነ፣ ስለ አማላጅ እና ተማላጅ እውነታ፣ የነገሮች ሁሉ አዋቂ መሆኑን፣ ሁሉን ጠባቂ እና በሰማያት እና በምድር ያሉትን ሁሉ መጠበቅ እንደማይከብደው፣ እሱ አላህ የሁሉ በላይ ታላቅ መሆኑን በውስጧ አቅፋለች።

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَخۡفَىٰ عَلَيۡهِ شَيۡءٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا فِي ٱلسَّمَآءِ ٥ هُوَ ٱلَّذِي يُصَوِّرُكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡحَامِ كَيۡفَ يَشَآءُۚ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٦ ﴾ آل عمران: ٥ - ٦

[5] አየቱል ኩርሲይ በመባል ትታወቃለች። ነብዩ (ﷺ) አየቱል ኩርሲን አንብቦ የተኛ ሰው ከሸይጧን እንደሚጠበቅ ነግረውናል። ነብዩ (ﷺ) ከእያንዳንዱ ፈርድ (ግዴታ) ሰላት በኋላ አየቱል ኩርሲይን ያነበበ ሰው በእርሱና ጀነት በመግባት መካከል የሚቀረው መሞቱ ብቻ ነው ብለዋል። ማለትም ሰውየው አየቱል ኩርሲን ከእያንዳንዱ ፈርድ ሰላት በኋላ ቢያነባት እና በዚህም ሁኔታው ቢሞት የጀነት ይሆናል ማለት ነው።

<u>አላህ</u> <u>በምድርም በሰማይም ምንም ነገር በርሱ ላይ አይሰወርም</u>። <u>እርሱ ያ በማሕጸኖች ውስጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነው</u>። <u>ከእርሱ በስተቀር በሐቅ የሚመለክ ሌላ አምላክ የለም</u>። <u>አሸናፊው ጥበበኛው ነው</u>። [አል-ኢምራን 5-6]

*በዚህ አንቀፅ ደግሞ በሐቅ የሚመለከው **<u>አላህ በሰማይም ይሁን በምድር ምንም ነገር እንደማይደበቀው</u>፣ <u>ከእናቶቻችን ማህፀን ውስጥ እንደፈለገ የሚቀርፀን</u>** መሆኑን ነገረን። **የሰው ልጅ ጨለማን ተገን አድርጎ ወይን ከሰዎች ተገለሎ የሰራውን ቢሰራ ከእርሱ ምንም የማይደበቀው <u>አላህ ከአርሹ በላይ ሆኖ ሁሉን ያውቃል፣ ያያል፣ ይሰማል</u>። ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ)[6] “የትም ብትሆን አላህን ፍራው” ብለዋል።***

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ لَيَجۡمَعَنَّكُمۡ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ لَا رَيۡبَ فِيهِۚ وَمَنۡ أَصۡدَقُ مِنَ ٱللَّهِ حَدِيثٗا ٨٧ ﴾ النساء: ٨٧

<u>አላህ</u> <u>ከእርሱ በስተቀር አምላክ የለም</u>። <u>ወደ ትንሣኤ ቀን በርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲኾን በእርግጥ ይሰበስባችኋል</u>። <u>በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማነው</u>? [አል-ኒሳዕ 87]

*ሁላችንን የቂያማ (ትንሳኤ) ቀን እንደሚሰበስበን አላህ ነገረን። ሙቶ በመቀስቀስ ማመን ከእምነት ማዕዘናት ውስጥ አንዱ ነው። ሙቶ በመቀስቀስ ያስተባበለ ከሃዲ ነው። **<u>ሙቶ በመቀስቀስ ያመነ፣ ለሰራው ሂሳብ ከፍያ እንዳለ አውቆ እዚህ ምድር ላይ እያለ ሰሚቀጥለው አለም ይዘጋጃል</u>።***

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ لَهُ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰ ٨ ﴾ طه: ٨

<u>አላህ</u> <u>ከእርሱ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም</u>። <u>ለእርሱ መልካሞች የኾኑ ስሞች አልሉት</u>። [ጣሃ 8]

አላህ መልካም ሰሞች እንዳሉት ነገረን። ሰሞቹን ባወቅን ቁጥር፣ ሰለ እሱ ያለን እውቀት እየጨመረ ይሄዳል። አላህን ልናውቀው የምንችለውም ለአላህ ያሉትን ሰሞችና ባህሪያት በትክክል ሰናውቅ ነው። አላህ እውቀትን ይጨምርልን።

[6] ሀዲሱ መዓዝ ኢብን ጀበል ያሥተላለፉትና ቱርሚዝይ የዘገቡት ሐዲስ ነው።

﴿ إِنَّنِيٓ أَنَا ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدۡنِي وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ لِذِكۡرِيٓ ١٤ ﴾ طه: ١٤

“<u>እኔ አላህ እኔ ነኝ ያለ እኔ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለምና ተገዛኝ</u>። ሶላትንም (በእርሷ) እኔን ለማውሳት ስገድ። [ጣሃ 14]

አላህ ነብዩላህ ሙሳን (ኣለይሂ ሰላም) በሐቅ የሚመለከው እርሱ መሆኑን እና ሰላትን እርሱን ለማስታወስ እንዲያቋቁሙ እና እንዲሰግዱ አዘዛቸው። ሰላት ለነብያችን (ﷺ) ህዝቦች ብቻ ሳይሆን የተደነገገው ከእኛ በፊት ለነበሩ ህዝቦችም ተደንግጎ ነበር።

﴿ وَهُوَ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ لَهُ ٱلۡحَمۡدُ فِي ٱلۡأُولَىٰ وَٱلۡأٓخِرَةِۖ وَلَهُ ٱلۡحُكۡمُ وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ٧٠ ﴾ القصص: ٧٠

<u>እርሱም አላህ ነው</u>። <u>ከእርሱ በስተቀር በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም</u>። ምስጋና በመጀመሪያይቱም በመጨረሻይቱም ዓለም ለእርሱ ብቻ ነው። ፍርዱም የእርሱ ብቻ ነው። ወደእርሱም ትመለሳላችሁ። [አል ቀሶስ 70]

በዚህ አንቀፅ ደግሞ ብቸኛው በሐቅ ተመላኪ፣ የፍርዱ ቀን ባለቤት፣ ወደ እርሱ ተመልሰን በእኛ መሃል ፍርድን የሚሰጠን፣ በመጀመሪያይቱም በመጨረሻይቱም አለም ምስጋና የሚገባው ለእርሱ ብቻ መሆኑን አላህ ነገረን።

﴿ لَّٰكِنَّا۠ هُوَ ٱللَّهُ رَبِّي وَلَآ أُشۡرِكُ بِرَبِّيٓ أَحَدٗا ٣٨ وَلَوۡلَآ إِذۡ دَخَلۡتَ جَنَّتَكَ قُلۡتَ مَا شَآءَ ٱللَّهُ لَا قُوَّةَ إِلَّا بِٱللَّهِۚ إِن تَرَنِ أَنَا۠

أَقَلَّ مِنكَ مَالٗا وَوَلَدٗا ٣٩ ﴾ الكهف: ٣٨ - ٣٩

“<u>እኔ ግን እርሱ አላህ ጌታዬ ነው፤ (እላለሁ)</u>። <u>በጌታዬም አንድንም አላጋራም</u>። “አትከልትህንም በገባህ ጊዜ አላህ የሻው ይኾናል፤ <u>በአላህ ቢኾን እንጂ ኀይል የለም፤</u> አትልም ኖሯልን! እኔን በገንዘብም በልጅም ካንተ በጣም ያነስኩ ሆኜ ብታየኝ። [አል ከህፍ 38-39]

በእኛ ላይ ግዴታ የሆነው እርሱን ብቻ ማወቅ እና ያዘንን ተግባር መፈፀም ብቻ ሳይሆን በእርሱ ላይ አንድንም አለማጋራትንም በጥብቅ ተከልክለናል። ምክንያቱም ማጋራት

ማለት አላህን እያመለኩ ከእርሱ ውጭ ያሉትን አካላት ከእርሱ ጋር አብሮ ማምለክ ማለት ነውና።

﴿ قُلۡ أَرُونِيَ ٱلَّذِينَ أَلۡحَقۡتُم بِهِۦ شُرَكَآءَ كَلَّاۚ بَلۡ هُوَ ٱللَّهُ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٢٧ ﴾ سبأ: ٢٧

“እነዚያን ተጋሪዎች አድርጋችሁ በእርሱ ያስጠጋችኋቸውን (ጣዖታት) አሳዩኝ። ተዉ (አታጋሩ)፤ <u>በእውነቱ እርሱ አሸናፊው ብልሃተኛው አላህ ነው</u>” በላቸው። [ሰበእ 27]

አታጋሩ ብሎ አላህ ገሰፀ፤ ምክንያቱም አሸናፊው አላህ ነውና። ሁሉን ማድረግ የሚችል፣ ብቸኛው ፈጣሪ ነውና። <u>አጋሪያን የሚያጋሯቸው ፍጡራን ናቸው</u>። <u>ፍጡራን ሁሉ ደግሞ ከአንድ አምላክ አላህ ፈላጊ ናቸው</u>።

﴿ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۖ يُكَوِّرُ ٱلَّيۡلَ عَلَى ٱلنَّهَارِ وَيُكَوِّرُ ٱلنَّهَارَ عَلَى ٱلَّيۡلِۖ وَسَخَّرَ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ

كُلٞ يَجۡرِي لِأَجَلٖ مُّسَمّٗىۗ أَلَا هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡغَفَّارُ ٥ ﴾ الزمر: ٥

<u>(አላህ) ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ</u>። <u>ሌሊትን በቀን ላይ ይጠቀልላል</u>። <u>ቀንንም በሌሊት ላይ ይጠቀልላል</u>፤ <u>ፀሐይንና ጨረቃንም ገራ</u>። ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ። ንቁ! <u>እርሱ አሸናፊው መሓሪው ነው</u>። [አል ዙመር 5]

ጌታችሁ አላህ ነው። እሱን ብቻ እንጂ ከእሱ ውጭ ሌላን አትገዙ (አታምልኩ)

*ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቁርአናዊ አንቀፆች ደግሞ <u>**የአላህን ጌትነት በመጠቆም አምልኮም ለእርሱ ብቻ እንደሚገባው የሚያስረግጡ ናቸው**</u>። ጌታ የሚለው ቃል <u>ፈጣሪ</u>፣ <u>ተንከባካቢ</u>፣ <u>ሰጪ</u>፣ <u>ነሺ</u>፣ <u>ህያው ሊድራጊ</u>፣ <u>ገዳይ</u> የሚሉትን ሰለሚይዝ ይህን ብቻ ማድረግ የሚችለው ደግሞ <u>ብቸኛው ፈጣሪ አንድ አላህ ብቻ ነው</u>። ታድያ ይህ ከሆነ እውነታው <u>**በትክክል አምልኮ የሚገባው ለብቸኛው ጌታ**</u>፣ <u>**ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ ለሆነው አንድ አላህ ብቻ እና ብቻ ነው**</u>። አምልኮ ማለት <u>በልብ የሚቋጠር</u>፣ <u>በምላስ የሚነገር</u>፣ <u>በሰውነት</u>*

<u>የሚተገበር ሲሆን</u> **<u>አላህ የሚወደው ሁሉ አምልኮ በመባል ይጠራል</u>**። ከአምልኮ ምሳሌዎች መካከል **<u>ፀሎት</u>**፣ **<u>ሰግደት</u>**፣ **<u>መመካት</u>**፣ **<u>መሰዋት</u>**፣ **<u>መፍራት</u>**፣ **<u>መተናነስ</u>** እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። **<u>እነዚህ ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆኑት ለብቸኛው ፈጣሪ፣ ለአንድ አምላክ አላህ ብቻ እና ብቻ ነው</u>**። **<u>ብቻውን የፈጠር በብቸኝነት ተመላኪ እሱ ብቻ ነው</u>**።

﴿ ٱللَّهَ رَبَّكُمۡ وَرَبَّ ءَابَآئِكُمُ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٢٦ ﴾ الصافات: ١٢٦

<u>አላህን ጌታችሁንና የቀድሞዎቹ አባቶቻችሁን ጌታ (ትተዋላችሁን)</u>? [አል ሷፋት 127]

የሰው ልጆች ሁሉ አባት አደም (አለይሂ ሰላም) ናቸው። አላህ የእኛ ብቻ ጌታ ሳይሆን ከእኛ በፊት የነበሩትም ጭምር እንደሆነ በማስረገጥ **<u>አምልኮ ለእርሱ ብቻ እንደሚገባ አንቀፁ ይጠቁማል</u>**።

﴿ خَلَقَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ ثُمَّ جَعَلَ مِنۡهَا زَوۡجَهَا وَأَنزَلَ لَكُم مِّنَ ٱلۡأَنۡعَٰمِ ثَمَٰنِيَةَ أَزۡوَٰجٖۚ يَخۡلُقُكُمۡ فِي بُطُونِ أُمَّهَٰتِكُمۡ خَلۡقٗا

مِّنۢ بَعۡدِ خَلۡقٖ فِي ظُلُمَٰتٖ ثَلَٰثٖۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمۡ لَهُ ٱلۡمُلۡكُۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ فَأَنَّىٰ تُصۡرَفُونَ ٦ ﴾ الزمر: ٦

<u>(አላህ) ከአንዲት ነፍስ ፈጠራቸሁ</u>። **<u>ከዚያም ከእርሷ መቀናጆዋን አደረገ</u>**። ለእናንተም ከግመልና ከከብት፣ ከፍየል፣ ከበግ ስምንት ዓይነቶችን (ወንድና ሴት) አወረደ። በእናቶቻችሁ ሆዶች ውስጥ በሦስት ጨለማዎች ውስጥ ከመፍጠር በኋላ (ሙሉ) መፍጠርን ይፈጠራቸኋል። ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ስልጣኑ የርሱ ብቻ ነው። ከእርሱ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም። ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ ይለናል!!! [አል ዙመር 6]

አላህ ከላይ የተዘረዘሩትን ፀጋዎች ሁሉ እኛ ለእኛ እንደዋለ፣ እሱ እንደሻውም እንደሚፈጥረን፣ ስልጣን ሁሉ ለእርሱ ብቻ እንደሆነ ነገረን። ይህን ሁሉ ማድረግ የሚችለው አንድ አምላክ አላህ ብቻ ሆኖ ሳለ ለምን በእርሱ ላይ ታጋሪላችሁ!!! ወዴትስ ትዞራላችሁ!!!

﴿ إِن تَكۡفُرُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنكُمۡۖ وَلَا يَرۡضَىٰ لِعِبَادِهِ ٱلۡكُفۡرَۖ وَإِن تَشۡكُرُواْ يَرۡضَهُ لَكُمۡۗ وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٞ وِزۡرَ أُخۡرَىٰۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُم مَّرۡجِعُكُمۡ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَۚ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٧ ﴾ الزمر: ٧

<u>ብትክዱ አላህ ከእናንተ የተብቃቃ ነው። ለባሪያዎቹም ከህደትን አይወድም። ብታመሰግኑም፤ እርሱን ይወድላችኋል። ማንኛይቱም ኃጢአትን ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ኃጢአት አትሸከምም። ከዚያም መመለሻቸሁ ወደ ጌታችሁ ነው። ትሠሩት የነበራችሁትንም ይነግራችኋል። እርሱ በልቦች ውስጥ ያሉትን ዐዋቂ ነውና።</u>
[አል ዙመር 7]

አላህ ለባርያዎቹ ከህደትን አይወድም፣ ብናመሰግነውም እርሱ ይወድልና። ፍጡራኑ አላህን ቢገዙ ለነፍሳቸው ጥቅም፣ ቢክዱም ነፍሳቸውን ነው የሚጎዱት። አላህ ከእኛም ከፍጡራኑ ሁሉም የተብቃቃ ነው። አላህ የፍጡራኑ ሁሉ መጠጊያ፤ በራሱ የተብቃቃ፤ ፍጡራኑን የሚያብቃቃ ነው።

﴿ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۖ رَبُّكُمۡ وَرَبُّ ءَابَآئِكُمُ ٱلۡأَوَّلِينَ ٨ ﴾ الدخان: ٨

<u>(አላህ) ከእርሱ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም። ሕያው ያደርጋል። ይገድላልም። ጌታችሁ የመጀመሪያዎቹ አባቶቻችሁም ጌታ ነው።</u> [አል ዱኻን 8]

አላህ በዚህ ቁርአናዊ አንቀፅ ከእርሱ በስተቀር በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደሌለ ሀያው ሉዳራጊ፤ ገዳይ፤ የእኛም ይሁን የአባቶቻችን ጌታ መሆኑን ተናገረ።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱعۡبُدُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ٢١ ﴾ البقرة: ٢١

<u>እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።</u> [አል-በቀራህ 21]

አላህ የሰው ልጆችን በጠቅላላ እንዲህ ሲል ይገሰፃል፣ ያዛል "<u>እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን የፈጠረውን ጌታችሁን ተገዙ (አምልኩ)</u>"። <u>የፍጡራኑ ሁሉ ፈጣሪ አንድ አምላክ አላህ ብቻ በመሆኑ አምልኮ ለእርሱ</u>

ብቻ ነው የሚገባው። ከእርሱ ውጭ ያሉት ሁሉ ፍጡር በመሆናቸው አምልኮት የሚገባቸው አካላት ሳይሆኑ አላህን እንዲያመልኩ ነው የተፈጠሩት። ***ከበደለኞች ሁሉ በደለኛ ማለት ፈጣሪን አላህን ትቶ ፍጡራንን የሚገዛ ነው***።

﴿ وَرَسُولًا إِلَىٰ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ أَنِّي قَدۡ جِئۡتُكُم بِـَٔايَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ أَنِّيٓ أَخۡلُقُ لَكُم مِّنَ ٱلطِّينِ كَهَيۡـَٔةِ ٱلطَّيۡرِ فَأَنفُخُ فِيهِ فَيَكُونُ طَيۡرَۢا بِإِذۡنِ ٱللَّهِۖ وَأُبۡرِئُ ٱلۡأَكۡمَهَ وَٱلۡأَبۡرَصَ وَأُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰ بِإِذۡنِ ٱللَّهِۖ وَأُنَبِّئُكُم بِمَا تَأۡكُلُونَ وَمَا تَدَّخِرُونَ فِي بُيُوتِكُمۡۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لَّكُمۡ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٤٩ ﴾ آل عمران: ٤٩

(ነብየላህ ኢሳን) ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል። (ይላልም)፡- "እኔ ከጌታዬ ዘንድ በተዓምር ወደ እናንተ መጣሁ። እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርፅ እፈጥራለሁ። በርሱም እተነፍስበታለሁ። በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል። በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፣ ለምጻኛንም አድናለሁ። ሙታንንም አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ። የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት።" [አል-ኢምራን 49]

ይህ አንቀፅ አላህ መልክተኞችን ታዓምር በመስጠት የሚልካቸው መሆኑን እና ከእነሱም መካከል ነብዩላህ ኢሳ አንዱ መሆናቸውን ያሳያል። ***ነብዩላህ ኢሳ የተሰጣቸው ታአምር በአላህ ፍቃድ መሆኑንም ገልፀዋል።*** *ይህም በዲኑ ላይ ወሰን ለለፉ ሁለት ፅንፎች መልስ ይሆና።* ***ኢሳን ለሚያመልኩ ነሷራዎች ኢሳ በአላህ ፍቃድ እንጂ በራሱ ምንም ታዓምራትን እንዳልፈፀመ፣ ኢሳን ለማይቀበሉት ብሎም በመጥፎ ሰም እሱንም እናቱንም ለሚያነሱት የሁዳዎች ደግሞ የአላህ ቅርብ ባለሚል እንደሆነ አላህ ታዓምራትን አስይዞ መላኩ በቂ ምላሽ ይሆናል።***

መልክተኞች ለህዝቦቻቸው ተአምራትን ቢያሳዩ መመሰገን የሚገባው ግን እነሱ ሳይሆኑ ተአምራትን አስይዞ እነሱን የላከው አንድ አምላክ አላህን ብቻ መሆን አለበት። አላህ ነብዩላህ ኢሳን (አለይሂ ሰላም) ታዓምራት አስይዞ እንደላከው ሁሉ፣ ለነብዩላህ ሙሳም (አለይሂ ሰላም)፣ ለነብዩላህ ሱለይማንም፣ ለነብዩላህ ኢብራሂምም (አለይሂ ሰላም)፣

ለነብዩ ሙሐመድም (ሶለይሂ ሰላቱ ወሰላም) እና ለሌሎችም መልክተኞቹ ታዓምራትን ሰጠይዞ ልኳል።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدۡ جَآءَكُمُ ٱلرَّسُولُ بِٱلۡحَقِّ مِن رَّبِّكُمۡ فَـَٔامِنُواْ خَيۡرٗا لَّكُمۡۚ وَإِن تَكۡفُرُواْ فَإِنَّ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمٗا ١٧٠ ﴾ النساء: ١٧٠

እናንተ ሰዎች ሆይ! መልክተኛው እውነትን ከጌታችሁ አመጣላችሁ። <u>እመኑም ለናንተ የተሻለ (ይኾናል)</u>። <u>ብትክዱም (አትጐዱትም)</u>። <u>በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነውና</u>። <u>አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው</u>። [አል-ኒሳዕ 17]

*መልክተኞች ለህዝቦቻቸው ይዘውት የመጡት ዋና መልክት **<u>አላህን በአምልኮ ኣንድ ኣድርጎ መገዛት፣ ከአላህ ውጭ አምልኮት የተሰጣቸውን አካላት ሁሉ መካድ ነው</u>**። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ በመሆኑ መልክተኛው ይዞ በመጣው መልእክት ብናምን ተጠቃሚዎቹ እኛው ነን። ብንክድም የምንጎዳው እኛ ነን።*

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدۡ جَآءَكُم بُرۡهَٰنٞ مِّن رَّبِّكُمۡ وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكُمۡ نُورٗا مُّبِينٗا ١٧٤ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَٱعۡتَصَمُواْ بِهِۦ فَسَيُدۡخِلُهُمۡ فِي رَحۡمَةٖ مِّنۡهُ وَفَضۡلٖ وَيَهۡدِيهِمۡ إِلَيۡهِ صِرَٰطٗا مُّسۡتَقِيمًا ١٧٥ ﴾ النساء: ١٧٤ - ١٧٥

እናንተ ሰዎች ሆይ! <u>ከጌታችሁ ዘንድ በእርግጥ አስረጅ መጣላችሁ</u>፤ ወደእናንተም ገላጭ የኾነን ብርሃን (ቁርኣንን) አወረድን። <u>እነዚያማ በአላህ ያመኑ በርሱም የተጠበቁ ከሱ በኾነው እዝነትና ችሮታ ውስጥ በእርግጥ ያስገባቸዋል</u>። <u>ወደእርሱም ቀጥተኛ መንገድን ይመራቸዋል</u>። [አል-ኒሳዕ 174-175]

﴿ يَسۡتَفۡتُونَكَ قُلِ ٱللَّهُ يُفۡتِيكُمۡ فِي ٱلۡكَلَٰلَةِۚ إِنِ ٱمۡرُؤٌاْ هَلَكَ لَيۡسَ لَهُۥ وَلَدٞ وَلَهُۥٓ أُخۡتٞ فَلَهَا نِصۡفُ مَا تَرَكَۚ وَهُوَ يَرِثُهَآ إِن لَّمۡ يَكُن لَّهَا وَلَدٞۚ فَإِن كَانَتَا ٱثۡنَتَيۡنِ فَلَهُمَا ٱلثُّلُثَانِ مِمَّا تَرَكَۚ وَإِن كَانُوٓاْ إِخۡوَةٗ رِّجَالٗا وَنِسَآءٗ فَلِلذَّكَرِ مِثۡلُ حَظِّ ٱلۡأُنثَيَيۡنِۗ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمۡ أَن تَضِلُّواْۗ وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمُۢ ١٧٦ ﴾ النساء: ١٧٦

ይጠይቁሃል በላቸው፡- "ወላጅና ልጅ ሳይኖረው በሚወረስ ሰው አላህ ይነግራችኋል። ለእርሱ ልጅ የሌለው ሰው ቢሞት ለእርሱም እኅት ብትኖረው ለእርስዋ ከተወው በረጀት (ትቶች ከሞተው ንብረት፣ ካለው ቀሪ ንብረት) ግማሹ አላት። እርሱም ለርሷ ልጅ የሌላት እንደኾነች (በሙሉ) ይወርሳታል። ሁለት (እኅቶች ወይም ከሁለት በላይ) ቢኾኑም ከተወው በረጀት ከሦስት ሁለት እጁ አላቸው። ወንድሞች (ና እኅቶች) ወንዶችና ሴቶች ቢኾኑም ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ብጤ አለው። <u>አላህ እንዳትሳሳቱ ለእናንተ ያብራራል</u>። <u>አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው</u>።" [አል-ኒሳዕ 176]

አላህ የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑን፣ እኛ እንዳንሳሳት እያንዳንዱን ነገር ማብራራቱን በዚህ አንቀፅ ላይ ተናገረ። ሁሏም ነፍስ ሞትን ቀማሽ ናት፣ አንድ ሰው ከሞት በኋላ ያሉት ንብረቶቹ በህይወት ላሉ የቅርብ ዘመዶቹ እንዴት መከፋፈል እንዳለበት፣ እያንዳንዱን ዝርዝር የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪ በማይሻረው ህጉ ላይ አስቀመጠ። የጋብቻ ኒካህ በአላህ ሸሪኣ ይፈፀም እንደሚባለው ሁሉ፣ ሰው ሲሞትም ንብረት ክፍፍል ሊደረግ የሚገባው ሙሉ በሆነው በአላህ ሸሪኣዊ ህግ መሆን አለበት።

﴿ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ خَٰلِقُ كُلِّ شَيْءٍ فَٱعْبُدُوهُۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ وَكِيلٌ ١٠٢﴾

الأنعام: ١٠٢

<u>ይህ ጌታችሁ አላህ ነው</u>። <u>ከእርሱ በቀር በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም</u>። <u>ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው</u>። <u>ስለዚህ እርሱን ብቻ ተገዙት</u>። <u>እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው</u>። [አል-አንዓም 102]

ይህቺ አንቀፅ የሚከተሉትን ታላላቅ ቁምነገሮች አቅፋለች

1) አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪና ጌታ መሆኑን፣

2) ከእርሱ በቀር በሐቅ የሚመለክ አምላክ የሌለ መሆኑን፣

3) እርሱን ብቻ ተገዙት እና አምልኩት የሚል ትእዛዝና ድንጋጌ፣

4) እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ መሆኑን፣

5) በሰማይም በምድርም ያለ ሁሉ የእርሱ ንብረት መሆኑንም ትገልፃለች።

﴿ لَّا تُدۡرِكُهُ ٱلۡأَبۡصَٰرُ وَهُوَ يُدۡرِكُ ٱلۡأَبۡصَٰرَۖ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ١٠٣ ﴾ الأنعام: ١٠٣

<u>ዓይኖች አያገኙትም</u>። <u>እርሱም ዓይኖችን ያያል</u>። <u>እርሱም ርኅራኄው ረቂቁ ውስጠ ዐዋቂው ነው</u>። [አል-አንዓም 103]

﴿ قَدۡ جَآءَكُم بَصَآئِرُ مِن رَّبِّكُمۡۖ فَمَنۡ أَبۡصَرَ فَلِنَفۡسِهِۦۖ وَمَنۡ عَمِيَ فَعَلَيۡهَاۚ وَمَآ أَنَا۠ عَلَيۡكُم بِحَفِيظٖ ١٠٤ ﴾ الأنعام: ١٠٤

“<u>ከጌታችሁ ዘንድ ብርሃኖች በእርግጥ መጡላችሁ። የተመለከተም ሰው (ጥቅሙ) ለነፍሱ ብቻ ነው። የታወረም ሰው (ጉዳቱ) በራሱ ላይ ብቻ ነው</u>። እኔም በእናንተ ላይ ጠባቂ አይደለሁም” (በላቸው)። [አል-አንዓም 104]

﴿ ۞ قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗاۖ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُم مِّنۡ إِمۡلَٰقٖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكُمۡ وَإِيَّاهُمۡۖ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَۖ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ١٥١ ﴾ الأنعام: ١٥١

“ኑ፤ <u>ጌታችሁ በእናንተ ላይ እርም ያደርገውን ነገር (በእርሱም ያዘዛችሁን) ላንብብላችሁ</u>” በላቸው። “<u>በእርሱ (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ</u>። ለወላጆችም በጎን ሥራ (ሥሩ)። ልጆቻችሁንም ከድህንት (ፍራቻ) አትግደሉ። እኛ እናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና። መጥፎ ሥራዎችንም ከእርሷ የተገለጸውንም የተደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ። ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢኾን እንጅ አትግደሉ። <u>ይህን ታውቁ ዘንድ (አላህ) በእርሱ አዘዛችሁ</u>።” [አል-አንዓም 151]

አላህ ለመልክተኛው ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባወረደው ቁርዓን ላይ ቃሉን እንዲያስተላልፉ በል፣ በላቸው እያለ ትዕዛዛትን ማስተላለፉ። ይህ ቁርአን የአላህ ቃል ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው። እዚህ አንቀፅ ላይ አላህ የራሱን እና የፍጡራንን መብት

የሚያስጠብቁ መመሪያዎችን አውርዷል። አላህ የሚከተሉትን መልካም እና ሰናይ ተግባራት ፍጡራኖችን ሲያዝ ነጂና መጥፎ ተግባራትን ደግሞ በተጓዳኝ ከልክሏል

1) <u>በአላህም ላይ ማንንም፣ ምንንም ነገር አታጋሩ</u>፣

2) ለወላጆቻችሁ በጎን ዋሉ፣

3) እናንተንም እነሱንም የሚመግበው አላህ ብቻ ነውና፣ ልጆቻችሁን ድህነት ፈርታችሁ አትግደሉ፣

4) መጥፎ ሰራዎችን በድብቅ በግልፅም የሚሰሩትን አትቅረቡ፣

5) ነፍስን ያለ አግባብ አታጥፉ፣

﴿ وَلَا تَقْرَبُوا۟ مَالَ ٱلْيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِى هِىَ أَحْسَنُ حَتَّىٰ يَبْلُغَ أَشُدَّهُۥ ۖ وَأَوْفُوا۟ ٱلْكَيْلَ وَٱلْمِيزَانَ بِٱلْقِسْطِ ۖ لَا نُكَلِّفُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا ۖ وَإِذَا قُلْتُمْ فَٱعْدِلُوا۟ وَلَوْ كَانَ ذَا قُرْبَىٰ ۖ وَبِعَهْدِ ٱللَّهِ أَوْفُوا۟ ۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ ﴿١٥٢﴾ ﴾

الأنعام: ١٥٢

“የየቲምንም ገንዘብ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጅ አትቅረቡ። ስፍርንና ሚዛንንም በትክክሉ ሙሉ። ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም። በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢኾንም እንኳ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ። በአላህም ቃል ኪዳን ሙሉ። እነሆ ትገሰጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ።” [አል-አንዓም 152]

አላህ በዚህ አንቀፅ ደግሞ የሚከተለውን መመሪያ አወረደ።

1) የየቲምን ገንዘብ ለመልካም ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር አትቅረቡ፣

2) ሰፍርን እና ሚዛንን ሌታጓድሉ፣

3) ነፍስን የአቅሟን ወይንም የችሎታዋን እንጂ አላህ እንደማያስገድዳት፣

4) በዘመዶቻችንም ላይ ቢሆን ፍትሃዊ ፍርድን መስጠት እንዳለብን፣

5) የገባነውን ቃል ኪዳን መሙላት እንዳለብን አዘዘ።

﴿ وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِي مُسْتَقِيمًا فَٱتَّبِعُوهُ ۖ وَلَا تَتَّبِعُوا۟ ٱلسُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمْ عَن سَبِيلِهِۦ ۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٥٣﴾ ﴾ الأنعام: ١٥٣

“ይህም ቀጥተኛ ሲኾን መንገዴ ነው፤ ተከተሉትም። (የጦሞት) መንገዶችንም አትከተሉ። ከ(ቀጥተኛው) መንገዱ እናንተን ይለያዩዋችኋልና።እነሆ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ።” [አል-አንዓም 153]

በዚህ አንቀፅ የሐቅ እና የጥመት መንገዶች የተለዩበት ነው። ቀጥተኛው መንገድ አንድ ሲሆን እሱም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) እና ሰሃባዎች (ባልደረባዎቻቸው) የነበሩበት መንገድ ነው። መዳንን እና ዋስትና የፈለገ ሰው ይህንን ቀጥተኛ መንገድ ብቻ ነው እንዲከተለው የታዘዘው። የተቀሩትን የጥመት መንገዶች አትከተሉ በማለት ከለከለን። ምክንያቱም ከሐቅ በኋላ ጥመት እንጂ ምን አለ? የጥመት መንገድ እኛን አንድ ከማድረግ ይልቅ ይለያየናል።

ከዚህ አንቀፅ የምንረዳቸው ነጥቦች

1) የሐቅ መንገድ አንድ ብቻ መሆኗን፣

2) እሷን እንድንከተል መታዘዛችን፣

3) ከአንዷ የሐቅ ጎዳና ውጭ ያሉት የጥመት መንገዶች በርካታ መሆናቸው፣

4) እነዚህን የጥመት መንገዶች አትከተሉ፣ እንዳንከተል ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ፣

5) የጥመት መንገዶች ከቀጥተኛው መንገድ ሊለዩን እንደሚችሉ አላህ ማስጠንቀቁ።

﴿ ثُمَّ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ تَمَامًا عَلَى ٱلَّذِىٓ أَحْسَنَ وَتَفْصِيلًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً لَّعَلَّهُم بِلِقَآءِ رَبِّهِمْ يُؤْمِنُونَ ﴿١٥٤﴾ ﴾ الأنعام: ١٥٤

ከዚያም ለሙሳ በዚያ መልካም በሠራው ላይ (ጸጋችንን) ለማሟላት ነገርንም ሁሉ ለመዘርዘር መጽሐፉን (ለእስራኤል ልጆች) መሪና እዝነት ይኾን ዘንድ ሰጠነው። እነርሱ በጌታቸው መገናኘት ሊያምኑ ይከጀላልና። [አል-አንዓም 154]

﴿ وَهَٰذَا كِتَٰبٌ أَنزَلْنَٰهُ مُبَارَكٌ فَٱتَّبِعُوهُ وَٱتَّقُوا۟ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ﴿١٥٥﴾ ﴾ الأنعام: ١٥٥

ይህም ያወረድነው የኾነ የተባረከ መጽሐፍ ነው። ተከተሉትም። ይታዘንላችሁም ዘንድ (ከክህደት) ተጠንቀቁ። [አል-አንዓም 155]

ይህ አንቀፅ ቁርዓን የአላህ ቃል ለመሆኑ እና ከእርሱ የወረደ ለመሆኑም ማስረጃ ነው።

﴿ أَن تَقُولُوٓا۟ إِنَّمَآ أُنزِلَ ٱلْكِتَٰبُ عَلَىٰ طَآئِفَتَيْنِ مِن قَبْلِنَا وَإِن كُنَّا عَن دِرَاسَتِهِمْ لَغَٰفِلِينَ ﴿١٥٦﴾ ﴾ الأنعام: ١٥٦

"(ያወረድነውም) መጽሐፍ የተወረደው ከፊታችን በሁለቱ ጭፍሮች ላይ ብቻ ነው። እኛም ከንባባቸው ዘንጊዎች ነበርን" እንዳትሉ ነው። [አል-አንዓም 156]

ይህ ቁርኣን የመካ ኢጋሪዎች ይቅርና ኢይሁዶችንም ነሷራዎችንም የሚመለከት ለእለማት እዝነት የወረደ መፀሃፍ መሆኑን አላህ አበክሮ ገለፀ። ቁርኣን በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ላይ በወረደበት ወቅት የአረብ ኢጋሪዎች፣ የሁዳዎች፣ ነሷራዎች ከሰውም አልፎ ጂኖች ነበሩ። ይህ የቁርኣን መልእክት ለሰው ልጅ እና ለጂኖች ባጠቃላይ ወረደ።

﴿ أَوْ تَقُولُوا۟ لَوْ أَنَّآ أُنزِلَ عَلَيْنَا ٱلْكِتَٰبُ لَكُنَّآ أَهْدَىٰ مِنْهُمْ ۚ فَقَدْ جَآءَكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَهُدًى وَرَحْمَةٌ ۚ فَمَنْ أَظْلَمُ

مِمَّن كَذَّبَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَصَدَفَ عَنْهَا ۗ سَنَجْزِى ٱلَّذِينَ يَصْدِفُونَ عَنْ ءَايَٰتِنَا سُوٓءَ ٱلْعَذَابِ بِمَا كَانُوا۟ يَصْدِفُونَ ﴿١٥٧﴾ ﴾

الأنعام: ١٥٧

ወይም "እኛ መጽሐፍ በእኛ ላይ በተወረደ ኖሮ ከእነሱ ይበልጥ የተመራን እንኾን ነበር" እንዳትሉ ነው። ስለዚህ ከጌታችሁ ግልጽ ማስረጃ፣ መምሪያም፣ እዝነትም በእርግጥ መጣላችሁ። በአላህም አንቀጾች ካስተባበለና ከእርሷም ከዞረ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን

ነው!!! እነዚያን አንቀጾቻችንን የሚተውትን ይተውት በነበሩት ምክንያት ብርቱን ቅጣት በእርግጥ እንቀጣቸዋለን። [አል-አንዓም 157]

ይህ አንቀፅ ደግሞ ቁርአን ከአላህ የተወረደ የመጨረሻ መፀሀፍ እንደሆነ ለአለማት እዝነት በመሆኑ ማንም ሰው ሊያስተባብለው እንደማይገባ ይገልፃል። በተጨማሪ በእኛ ላይ ቢወርድ ኖሮ እያሉ ምክንያት የሚደረድሩ ሰዎች ምክንያት እንደማይሰጣቸው እና ይልቁንም በቁርአን መመሪያ ካልተመሩ ብርቱ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ያስጠነቅቃል።

﴿ قُلْ أَغَيْرَ ٱللَّهِ أَبْغِى رَبًّا وَهُوَ رَبُّ كُلِّ شَىْءٍ ۚ وَلَا تَكْسِبُ كُلُّ نَفْسٍ إِلَّا عَلَيْهَا ۚ وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَىٰ ۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُم مَّرْجِعُكُمْ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ ﴿١٦٤﴾ ﴾ الأنعام: ١٦٤

በላቸው "<u>እርሱ (አላህ) የሁሉ ጌታ ሲኾን ከአላህ በቀር (በስተቀር) ሌላን ጌታ እፈልጋለሁን</u>!!! ነፍስም ሁሉ በራሷ ላይ እንጅ (ክፉን) አትሠራም። ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላይቱን ሸክም (ኃጢአት) አትሸከምም። <u>ከዚያም መመለሻችሁ ወደ ጌታችሁ ነው</u>። ወዲያውም በእርሱ ትለያዩበት የነበራችሁትን ሁሉ ይነገራችኋል።" [አል-አንዓም 164]

የመካ ኢጋሪያን የአላህ መልከተኛ (ﷺ) "<u>አንድ አመት ያንተን ጌታ እንገዛ አንድ አመት የእኛን ጌቶች ተገዛ</u>" ብለው ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር። አላህ ደግሞ "<u>እርሱ አላህ የሁሉ ጌታ ሲሆን ከአላህ ሌላ ጌታ እፈልጋለሁን?</u>" የሚል ምላሽ እንዲሰጡ አዘዛቸው። እያንዳንዱ ነፍስ ለሰራው መጥፎ ስራ ተጠያቂው እራሱ ይሆናል። ማንም የማንንም ሀጢያት አይሸከምም። የአባት ሀጢያት ወደ ልጅ ይተላለፋል የሚባል ነገር በኢስላም አይሰራም። ሁሉም ፍጡር የምፅአት ቀን ወደ ጌታችን አላህ ይመለሳል። እዚህ ምድር ላይ ስንለያይበት በነበሩ ጉዳዩች ላይ አጠቃላይ ፍርድ አላህ ይሰጣል።

﴿ رَّبُّكُمْ أَعْلَمُ بِمَا فِى نُفُوسِكُمْ ۚ إِن تَكُونُوا۟ صَٰلِحِينَ فَإِنَّهُۥ كَانَ لِلْأَوَّٰبِينَ غَفُورًا ﴿٢٥﴾ ﴾ الإسراء: ٢٥

<u>ጌታችሁ (አላህ) በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉ አዋቂ ነው</u>። ታዛጉችም ብትኾኑ (በመሳሳትም ብታጠፉ) እርሱ ለተመላሾች መሓሪ ነው። [አል ኢስራዕ 25]

አላህ ውስጥ አዋቂነቱንና ከወንጀላቸው ለተመለሱም መሐሪ መሆኑን ተናገረ።

﴿ رَّبُّكُمُ ٱلَّذِى يُزْجِى لَكُمُ ٱلْفُلْكَ فِى ٱلْبَحْرِ لِتَبْتَغُوا۟ مِن فَضْلِهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ كَانَ بِكُمْ رَحِيمًا ﴿٦٦﴾ ﴾ الإسراء: ٦٦

<u>ጌታችሁ (አላህ) ያ ከችሮታው ትፈልጉ ዘንድ መርከቦችን በባሕር ለይ ለእናንተ የሚነዳላችሁ ነው። እነሆ እርሱ ለናንተ አዛኝ ነውና።</u> [አል ኢስራዕ 66]

አዛኙ አላህ ባሮቹ ከችሮታው ይቋደሱ ዘንድ መርከቦችን በታላላቅ ባህሮች ላይ እንዲጓዙ አደረገ። ከአህጉር አህጉር ታላላቅ ባህሮችን እና ውቅያኖሶችን አቋርጠው ሰዎችን እና እቃዎችን የጫኑ መርከቦች በሰላም እንዲጓዙ በእዝነቱ እና በርህራሄው አገራቸው። ከእነዚህ ታላላቅ ባህር እና ውቅያኖሶች የሚነሱት ግዙፍ ማእበሎች መርከቦቹን መገልበጥ ይችሉ ነበር። ነገር ግን አላህ ለፍጡራኖቹ አዛኝ ነውና በሰላም ተነስተው በሰላም ከሚፈልጉበት ቦታ እንዲደርሱ አደረገ። ጌታችን አላህ ሆይ! ሰፍር ቁጥር የሌለው ምስጋና ላንተ ይገባህ። አንተንም ከልብ አመሰጋኝ ባሮች አድርገን። በፀጋህ ከማሰተባበልም አንተው ጠብቀን።

﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱرْكَعُوا۟ وَٱسْجُدُوا۟ وَٱعْبُدُوا۟ رَبَّكُمْ وَٱفْعَلُوا۟ ٱلْخَيْرَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٧٧﴾ ﴾

الحج: ٧٧

እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! <u>(በስግደታችሁ) አጎንብሱ፣ በግንባራችሁም ተደፉ፣ ጌታችሁንም ተገዙ፣ በጎንም ነገር ሥሩ፣ ልትድኑ ይከጀልላችኋልና።</u> [አል ሐጅ 77]

﴿ يُولِجُ ٱلَّيْلَ فِى ٱلنَّهَارِ وَيُولِجُ ٱلنَّهَارَ فِى ٱلَّيْلِ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ ۖ كُلٌّ يَجْرِى لِأَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ لَهُ ٱلْمُلْكُ ۚ وَٱلَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِهِۦ مَا يَمْلِكُونَ مِن قِطْمِيرٍ ﴿١٣﴾ ﴾ فاطر: ١٣

<u>ሌሊትን በቀን ውስጥ ያስገባል። ቀንንም በሌሊት ውስጥ ያስገባል፤ ፀሐይንና ጨረቃንም ገራ። ሁሉም እተወሰነ ጊዜ ድረስ ይሮጣሉ። ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ንግሥናው የእርሱ ብቻ ነው። እነዚያም ከእርሱ ሌላ የምትግገዟቸው የተምር ፍሬ ሽፋን እንኳ አይኖራቸውም።</u> [ፋጢር 13]

ጌታችን አላህ የሁሉ (ከአርሽ እስከ ፈርሽ [7]) ባለቤት እንደሆነ እና ከእርሱ ውጭ የሚገዟቸው የተምር ፍሬ ሽፋን እንኳ የመፍጠር አቅሙ የላቸውም።

﴿ إِن تَدۡعُوهُمۡ لَا يَسۡمَعُواْ دُعَآءَكُمۡ وَلَوۡ سَمِعُواْ مَا ٱسۡتَجَابُواْ لَكُمۡۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَكۡفُرُونَ بِشِرۡكِكُمۡۚ وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثۡلُ خَبِيرٖ ١٤ ﴾ فاطر: ١٤

<u>ብትጠሩዋቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም። ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም። በትንሣኤም ቀን (እነርሱን በአላህ) ማጋራታችሁን ይክዳሉ። እንደ ውስጠ ዐዋቂው (አላህ) ማንም አይነግርህም።</u> [ፋጢር 14]

ከዚህ አንቀፅ የምንወስደው ትምህርት

1) ከአላህ ውጭ የሚመለኩት የተጣሪዎቻቸውን ጥሪ እንደማይሰሙ፣

2) ቢሰሙም እንኳን መልስ ሊሰጡ እንደማይችሉ፣

3) እነዚህን የውሸት አማልክቶች የሚያመልክ ማንኛውም ሰው በሚቀጥለው አለምም ይሁን በእዚህ አለም ኪሳራ ላይ እንደሚወድቁ።

4) አምላኪና ተመላኪ እንደሚካካዱ እንገነዘባለን።

﴿ ۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ أَنتُمُ ٱلۡفُقَرَآءُ إِلَى ٱللَّهِۖ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلۡغَنِيُّ ٱلۡحَمِيدُ ١٥ إِن يَشَأۡ يُذۡهِبۡكُمۡ وَيَأۡتِ بِخَلۡقٖ جَدِيدٖ ١٦ وَمَا ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ بِعَزِيزٖ ١٧ ﴾ فاطر: ١٥ - ١٧

<u>እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁል ጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ። አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው። ቢሻ ያስወግዳችኋል። አዲስንም ፍጡር ያመጣል። ይህም በአላህ ላይ ምንም አስቸጋሪ አይደለም።</u> [ፋጢር 15-16]

[7] አርሽ ታላቁ የአላህ ፍጡር በመባል ይታወቃል። ፈርሽ ደግሞ ማለት 7ኛው ምድር ለማለት ነው። ከአርሽ ጀምሮ እስከ 7ኛው ምድር ድረስ ያለው ሁሉ ጌታው፣ ፈጣሪው፣ ተንከባካቢው አላህ ብቻ እና ብቻ ነው። ከአላህ ውጭ ያሉት ግን የተምር ሽፋን እንኳ አይመልኩም። ስለዚህም አምልኮ ለእርሱ ምሉዕ ስም እና ባህሪያት ላሉት የሁሉ ባለቤት ለሆነው ብቸኛው ፈጣሪ እና አምላክ አላህ ብቻ ይገባው።

የአላህን ችሮታ ከጃዬች እና ድሆች መሆናችንን ብሎም እርሱ በራሱ የተብቃቃ ምስጉን ጌታ መሆኑን ይነግረናል።

አላህ ስለመኖሩ ማስረጃዎች

ከዚህ በታች የሚመጡ አንቀፆች አላህ ስለመኖሩ የሚያረጋግጡ ናቸው። አላህን እዚህ ምድር ላይ ልናየው አንችልም። ከአማኞች ባህሪ አንዱ በፈጣሪነቱ፣ በታእምራቱ እና በአንቀፆቹ የሚታወቀውን አምላክ አላህ ሳያዩ ማመን ነው። የሚቀጥለው አለም ላይ ገነት ውስጥ ከመብላት ከመጠጣት እና ከሌሎችም መጠቃቀሚያዎች ይልቅ ታላቁ ፀጋ ጌታቸውን እና ፈጣሪያቸውን አላህን ማየት ነው። ከዚህም በታች ያሉ አንቀፆች አላህ ስለመኖሩ የሚጠቁሙ እና የሚያስረግጡ ናቸው።

﴿ سَنُرِيهِمۡ ءَايَٰتِنَا فِي ٱلۡأٓفَاقِ وَفِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُ ٱلۡحَقُّۗ أَوَلَمۡ يَكۡفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ﴿٥٣﴾ ﴾ فصلت: ٥٣

እርሱም (ቁርአን) እውነት መኾኑ ለእነርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ <u>በአድናቂቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን</u>። <u>ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ መኾኑ አይበቃቸውምን</u>? [ፉሲለት 53]

ለሰው ልጆች የጌታን መኖር ለማወቅ ቁርአን ዋናው ምንጭ ነው። ነገር ግን ቁርአንን ያልተቀበሉ ሰዎች በነፍሶቻቸው እና በተአምራት (ሰማያት፣ ምድሮች፣ ተራሮች፣ ባህሮች...) ውስጥ የብቸኛው ፈጣሪ አላህን መኖር የሚያመለክቱ አንቀፆች አሉ። በመቀጠልም አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ ነውና ይህን መገለጫውን ለሰው ልጆች እንዲገለፀውበት ተናገረ።

﴿ وَقُلِ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ سَيُرِيكُمۡ ءَايَٰتِهِۦ فَتَعۡرِفُونَهَاۚ وَمَا رَبُّكَ بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعۡمَلُونَ ﴿٩٣﴾ ﴾ النمل: ٩٣

ምስጋናም ለአላህ ነው። ተዓምራቶቹን ወደፊት ያሳያችኋል። "ታውቋታላችሁ" በላቸው። ጌታህም ከምትሠሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም። [አል ነምል 93]

አላህ ከሚታወቅባቸው ነገራቶች ውስጥ ተዓምራቶቹ ዋነኛ ናቸው። በዚህ አንቀፅ አላህ እራሱን እያስተዋወቀ ነው።

﴿ وَيُرِيكُمْ ءَايَٰتِهِۦ فَأَىَّ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ تُنكِرُونَ ﴿٨١﴾ ﴾ غافر: ٨١

ተዓምራቱንም ያሳያችኋል። ታዲያ ከአላህ ተዓምራት የትኛውን ትክዳላችሁ? [አል ጋፊር 81]

በአላህ ታዓምራት መካድ በአላህ እንደመካድ ነው። ታዓምራቱን ለፍጡራኖቹ በእርግጥ ያሳያል። እሱ ሁሉን ነገር በማድረግ ላይ ቻይ ነውና።

﴿ إِنَّ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱلْفُلْكِ ٱلَّتِى تَجْرِى فِى ٱلْبَحْرِ بِمَا يَنفَعُ ٱلنَّاسَ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ

ٱلسَّمَآءِ مِن مَّآءٍ فَأَحْيَا بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَا وَبَثَّ فِيهَا مِن كُلِّ دَآبَّةٍ وَتَصْرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ وَٱلسَّحَابِ ٱلْمُسَخَّرِ بَيْنَ

ٱلسَّمَآءِ وَٱلْأَرْضِ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿١٦٤﴾ ﴾ البقرة: ١٦٤

ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትንና ቀንንም በማተካካት፣ በዚያችም ሰዎችን በሚጠቅም ነገር (ተጭና) በባህር ላይ በምትንሻለለው ታንኳ (መርከብ)፣ አላህም ከሰማይ ባወረደው ውሃና በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው በማድረጉ፣ በርሷም ውስጥ ከተንቀሳቃሽ ሁሉ በመበተኑ፣ ነፋሶችንም (በየአቅጣጫው) በማገለባበጥ፣ በሰማይና በምድር መካከል በሚነዳውም ደመና ለሚያውቁ ሕዝቦች እርግጠኛ ምልክቶች አሉ። [አል-በቀራህ 163]

ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ለአእምሮ ባለቤቶች አላህ ለመኖሩ፣ ለመፍጠሩ እና በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ለመሆኑ ምልክቶች ናቸው።

﴿ إِنَّ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفِ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ لَءَايَٰتٍ لِّأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٠﴾ ﴾ آل عمران: ١٩٠

ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አሉ። [አል-ኢምራን 190]

አላህ ለአእምሮ ትልቅ ቦታ ሰጥቷል። አዋቂዎችን (የአእምሮ ባለቤቶች) የእርሱን ተአምራቶች በማየት የእሱን ጌትነት እና አምላክነት እንደሚያውቁ ተናገረ።

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجْنَا بِهِۦ نَبَاتَ كُلِّ شَىْءٍ فَأَخْرَجْنَا مِنْهُ خَضِرًا نُّخْرِجُ مِنْهُ حَبًّا مُّتَرَاكِبًا

وَمِنَ ٱلنَّخْلِ مِن طَلْعِهَا قِنْوَانٌ دَانِيَةٌ وَجَنَّٰتٍ مِّنْ أَعْنَابٍ وَٱلزَّيْتُونَ وَٱلرُّمَّانَ مُشْتَبِهًا وَغَيْرَ مُتَشَٰبِهٍ ۗ ٱنظُرُوٓا۟ إِلَىٰ ثَمَرِهِۦٓ إِذَآ أَثْمَرَ

وَيَنْعِهِۦٓ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكُمْ لَـَٔايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿٩٩﴾ ﴾ الأنعام: ٩٩

እርሱም (አላህ) ያ ከዳመና ውሃን ያወረደ ነው። በርሱም የነገሩን ሁሉ በቃይ አወጣን። የተደራረበንም ቅንጣት ከርሱ የምናወጣ የኾነን ለምለም (አዝመራ) ከርሱ አወጣን። ከዘንባባም ከእንቡጧ የተቀራረቡ የኾኑ ዘለላዎች አሉ። ከወይኖችም፣ ከወይራም፣ ከሩማንም (ቅጠላቸው) ተመሳሳይና (ፍሬያቸው) የማይመሳሰል ሲኾኑ አትክልቶችን (አወጣን)። ባፈራ ጊዜ ወደ ፍሬውና ወደ መብሰሉ ተመልከቱ። በእነዚህ ተዓምራት ለሚያምኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉ። [አል-አንዓም 99]

በዚህ አንቀፅ የእሱን መኖር ለማወቅ ምልክቶች ይሆኑን ዘንድ በርካታ ተአምራቶችን ፈጣሪያችን አላህ ነገረን።

﴿ هُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ لِتَسْكُنُوا۟ فِيهِ وَٱلنَّهَارَ مُبْصِرًا ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَـَٔايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ ﴿٦٧﴾ ﴾

يونس: ٦٧

እርሱ (አላህ) ያ ሌሊትን በውስጡ ልታርፉበት (ጨለማ)፤ ቀንንም (ልትሠሩበት) ብርሃን ያደረገላችሁ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሕዝቦች በእርግጥ ታምራቶች አሉ። [ዩኑስ 67]

አላህ ለአእምሮ ባለቤቶች፣ ለአማኞች፣ ለሚሰሙ ህዝቦች፣ ለሚያስተነትኑ ህዝቦች እና የመሳሰሉ አገላለፆች በመጠቀም የእርሱን ጌትነት፣ በነገሮች ሁሉ ቻይ መሆኑን እንድንገነዘብ ይመክረናል።

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِى مَدَّ ٱلْأَرْضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَٰسِىَ وَأَنْهَٰرًا ۖ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ جَعَلَ فِيهَا زَوْجَيْنِ ٱثْنَيْنِ ۖ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ

لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٣﴾ ﴾ الرعد: ٣

<u>እርሱም (አላህ) ያ ምድርን የዘረጋ በሷም ተራራዎችንና ወንዞችን ያደረገ በውስጧም ከፍሬዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ዓይነቶችን ያደረገ ነው</u>። ሌሊትን በቀን ይሸፍናል። <u>በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አሉ</u>። [አል-ረዕድ 3]

በትክክል ምርምር ለሚያደርጉ ህዝቦች ከላይ በጠቀሳቸው ታአምራቶች የአላህ አምላክነት በቀላሉ መረዳት ይችላሉ።

﴿ وَفِى ٱلْأَرْضِ قِطَعٌ مُّتَجَٰوِرَٰتٌ وَجَنَّٰتٌ مِّنْ أَعْنَٰبٍ وَزَرْعٌ وَنَخِيلٌ صِنْوَانٌ وَغَيْرُ صِنْوَانٍ يُسْقَىٰ بِمَآءٍ وَٰحِدٍ وَنُفَضِّلُ بَعْضَهَا

عَلَىٰ بَعْضٍ فِى ٱلْأُكُلِ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿٤﴾ ﴾ الرعد: ٤

በምድርም የተጎራበቱ ቁርጥራጮች አልሉ። ከወይኖችም አትክልቶች አዝርዕቶችም መንታዎችና መንታዎች ያልኾኑ ዘንባባዎችም አልሉ። በአንድ ውሃ ይጠጣሉ፤ (በጣዕምም ይለያያሉ)። ከፊሉዋንም በከፊሉ ላይ በሚበላው ሰብል እናበልጣለን። <u>በዚህም ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች ተዓምራት አለበት</u>። [አል-ረዕድ 4]

የአላህን መኖር ከምናቅባቸው መንገዶች ውስጥ ተአምራቶቹ ዋነኞቹ ናቸው። እዚህም አንቀፅ ላይ የአላህን በነገሮቹ ሁሉ ቻይ፣ አዋ የሌለው፣ ጥበበኛ፣ አሸናፊ መሆኑን እንገነዘባለን።

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزْقًا لَّكُمْ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ

ٱلْفُلْكَ لِتَجْرِىَ فِى ٱلْبَحْرِ بِأَمْرِهِۦ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلْأَنْهَٰرَ ﴿٣٢﴾ ﴾ إبراهيم: ٣٢

<u>አላህ ያ</u> <u>ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ</u> <u>ከሰማይም ውሃን ያወረደ</u> <u>በእርሱም ከፍሬዎች ሲሳይን ለእናንተ ያወጣ</u> <u>መርከቦችንም በፈቃዱ በባሕር ላይ ይንሻለሉ ዘንድ ለናንተ የገራ ወንዞችንም ለናንተ የገራ ነው</u>። [ኢብራሂም 32]

ከምንም በፊት አላህ ነበር። ከዛም ከእሱ ውጭ ያለውን ነገር ሁሉ ፈጠረ። ሰማያትና ምድርን ብቻውን የፈጠረ፣ ከሰማይ (ከዳመና) ዝናብን ያወረደ፣ ለእኛም ብቸኛው ሲሳይ ሊጋሽ እሱ ብቻ መሆኑን በዚህ እና በቀጣይ አንቀፆች እንገነዘባለን።

﴿ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ دَآئِبَيۡنِۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ ٣٣ ﴾ إبراهيم: ٣٣

ፀሐይንና ጨረቃንም ዘወትር ኼያጆች ሲኾኑ <u>ለእናንተ የገራ</u> ሌሊትንና ቀንንም <u>ለእናንተ የገራላችሁ ነው</u>። [ኢብራሂም 33]

እዚህም አንቀፅ ላይ ለእኛ የዋለውን ውለታ እየነገረን ነው። ከእሱ ውጭም ማንም ይህንን ሊያደርግልን እንደማይችል በአንቀፁ አስረግጦ ነግሮናል።

﴿ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۚ تَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٣ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِن نُّطۡفَةٖ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٞ مُّبِينٞ ٤ ﴾ النحل: ٣ - ٤

ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ። ሰውን ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው። ከዚያም እርሱ ወዲያውኑ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይኾናል። [አል ነሕል 3-4]

﴿ وَٱلۡأَنۡعَٰمَ خَلَقَهَاۚ لَكُمۡ فِيهَا دِفۡءٞ وَمَنَٰفِعُ وَمِنۡهَا تَأۡكُلُونَ ٥ وَلَكُمۡ فِيهَا جَمَالٌ حِينَ تُرِيحُونَ وَحِينَ تَسۡرَحُونَ ٦ ﴾ النحل: ٥ - ٦

ግመልን፣ ከብትን፣ ፍየልንም በርሷ (ብርድ መከላከያ) ሙቀት ጥቅሞችም ያሉባት ስትኾን ለእናንተ ፈጠረላችሁ። ከርሷም ትበላላችሁ። ለእናንተም በእርሷ ወደ ማረፊያዋ በምትመልሷት ጊዜ በምታሰማሩዋትም ጊዜ ውበት አላችሁ። [አል ነሕል 5-6]

﴿ وَتَحۡمِلُ أَثۡقَالَكُمۡ إِلَىٰ بَلَدٖ لَّمۡ تَكُونُواْ بَٰلِغِيهِ إِلَّا بِشِقِّ ٱلۡأَنفُسِۚ إِنَّ رَبَّكُمۡ لَرَءُوفٞ رَّحِيمٞ ٧ وَٱلۡخَيۡلَ وَٱلۡبِغَالَ وَٱلۡحَمِيرَ لِتَرۡكَبُوهَا وَزِينَةٗۚ وَيَخۡلُقُ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٨ ﴾ النحل: ٧ - ٨

ጉዞዎቻችሁንም በነፍሶች ችግር እንጂ ወደማትደርሱበት አገር ትሸከማለች። ጌታችሁ በእርግጥ ሩኅሩኅ አዛኝ ነውና። ፈረሶችንም፣ በቅሎዎችንም፣ አህዮችንም ልትቀመጡዋቸውና ልታጌጡባቸው (ፈጠረላችሁ)። <u>የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል</u>። [አል ነሕል 7-8]

አላህ ለእኛ ብዙ ነገሮችን ፈጥሮዋል። ለእኛ መጠቃቀሚያ የፈጠረልን ነገሮች ብዙ ናቸው። የማናውቃቸውን ድንቅ ነገሮች ይፈጥራል። በየዘመኑ ለእኛ የሚሆኑ ነገሮችን እና መገልገያዎችን ይፈጥርልናል።

﴿ وَعَلَى ٱللَّهِ قَصۡدُ ٱلسَّبِيلِ وَمِنۡهَا جَآئِرٞۚ وَلَوۡ شَآءَ لَهَدَىٰكُمۡ أَجۡمَعِينَ ٩ ﴾ النحل: ٩

በአላህም ላይ (በችሮታው) ቀጥተኛውን መንገድ መግለጽ አለበት። ከእርሷም (ከመንገድ) ጠማማ አልለ። በሻም ኖሮ ሁላችሁንም በእርግጥ ባቀናችሁ ነበር። [አል ነሕል 9]

﴿ هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ لَّكُم مِّنۡهُ شَرَابٞ وَمِنۡهُ شَجَرٞ فِيهِ تُسِيمُونَ ١٠ يُنۢبِتُ لَكُم بِهِ ٱلزَّرۡعَ وَٱلزَّيۡتُونَ وَٱلنَّخِيلَ وَٱلۡأَعۡنَٰبَ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِۗ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ١١ ﴾ النحل: ١٠ - ١١

እርሱ ያ ከዳመና ውሃን ያወረደ ነው። ከእርሱ ለእናንተ መጠጥ አላችሁ። ከእርሱም (እንስሳዎችን) በእርሱ የምታሰማሩበት ዛፍ (ይበቅልበታል)። በእርሱ ለእናንተ አዝመራን፣ (የዘይት) ወይራንም፣ ዘምባባዎችንም (ተምርን)፣ ወይኖችንም፣ ከፍሬዎችም ሁሉ ያበቅልላችኋል። <u>በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምር አልለ</u>። [አል ነሕል 10-11]

﴿ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ وَٱلنُّجُومُ مُسَخَّرَٰتُۢ بِأَمۡرِهِۦٓۗ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ﴿١٢﴾ ﴾ النحل: ١٢

<u>ለእናንተም ሌሊትንና ቀንን፣ ፀሐይንና ጨረቃንም ገራላችሁ።</u> <u>ከዋክብትም በፈቃዱ የተገሩ ናቸው።</u> <u>በዚህ ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምራቶች አልሉ።</u> [አል ነሕል 12]

﴿ وَمَا ذَرَأَ لَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُخۡتَلِفًا أَلۡوَٰنُهُۥٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّقَوۡمٖ يَذَّكَّرُونَ ﴿١٣﴾ ﴾ النحل: ١٣

በምድርም ላይ መልኮቹ የተለያዩ ኾኖ ለእናንተ የፈጠረላችሁን ሁሉ (ገራላችሁ)። <u>በዚህ ውስጥ ለሚገሰጹ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምር አልለ።</u> [አል ነሕል 13]

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِي سَخَّرَ ٱلۡبَحۡرَ لِتَأۡكُلُواْ مِنۡهُ لَحۡمٗا طَرِيّٗا وَتَسۡتَخۡرِجُواْ مِنۡهُ حِلۡيَةٗ تَلۡبَسُونَهَاۖ وَتَرَى ٱلۡفُلۡكَ مَوَاخِرَ فِيهِ وَلِتَبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِهِۦ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ﴿١٤﴾ ﴾ النحل: ١٤

<u>እርሱም (አላህ)</u> ያ ባሕርን ከእርሱ እርጥብ ስጋን (አሳን እና የባህር ውስጥ እንስሳት) ልትበሉና ከእርሱም የምትለብሱትን ጌጣጌጥ ታወጡ ዘንድ የገራ ነው። መርከቦችንም በውስጡ (ውሃውን) ቀዳጆች ኾነው (ሲንሻለሉ) ታያለህ። <u>ከችሮታው ልትፈልጉና ልታመሰግኑም (ገራላችሁ)</u>። [አል ነሕል 14]

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) "ባህር ውስጥ የሚኖሩ እንስሳዎች ሁሉ ለመብልነት የተፈቀዱ ናቸው።" ብለው ነግረውናል።

﴿ وَأَلۡقَىٰ فِي ٱلۡأَرۡضِ رَوَٰسِيَ أَن تَمِيدَ بِكُمۡ وَأَنۡهَٰرٗا وَسُبُلٗا لَّعَلَّكُمۡ تَهۡتَدُونَ ﴿١٥﴾ وَعَلَٰمَٰتٖۚ وَبِٱلنَّجۡمِ هُمۡ يَهۡتَدُونَ ﴿١٦﴾ ﴾ النحل: ١٥ - ١٦

(አላህ) በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለባት። ጂረቶችንም፣ መንገዶችንም ትመሩ ዘንድ (አደረገ)። ምልክቶችንም (አደረገ)። በከዋክብትም እነሱ ይምመራሉ። [አል ነሕል 15-16]

﴿ أَفَمَن يَخۡلُقُ كَمَن لَّا يَخۡلُقُۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ١٧ وَإِن تَعُدُّواْ نِعۡمَةَ ٱللَّهِ لَا تُحۡصُوهَآۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَغَفُورٞ رَّحِيمٞ ١٨ ﴾

النحل: ١٧ - ١٨

የሚፈጥር እንደማይፈጥር ነውን!!! አትገሰጹምን!!! የአላህንም ጸጋ ብትቆጥሩ አትዘልቋትም። አላህ በእርግጥ መሓሪ አዛኝ ነውና። [አል ነሕል 17-18]

አላህ በዚህ አንቀፅ ፈጣሪ መሆኑን ከእርሱ ውጭ ያሉት መፍጠር እንደማይችሉ፣ የእሱን ፀጋዎች ብንዘረዝር ቆጥረን እንደማንዘልቃቸው፣ አዛኝ እና መሓሪ መሆኑንም ገለፀ።

﴿ وَٱللَّهُ أَخۡرَجَكُم مِّنۢ بُطُونِ أُمَّهَٰتِكُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ شَيۡـٔٗا وَجَعَلَ لَكُمُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَٱلۡأَفۡـِٔدَةَۙ لَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ٧٨ ﴾ النحل: ٧٨

አላህም ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ። ታመሰግኑም ዘንድ ለእናንተ መስሚያን ማያዎችንም ልቦችንም አደረገላችሁ። [አል ነሕል 78]

አላህ እኛን የፈጠረን እሱን በብቸኝነት እንድናመልከው ነው። ከእናታችን ሆድ ሰንወጣ ምንም የማናውቅ ሆነን ወጣን። የተፈጠርንበትን አላማ እናሳካ ዘንድ፣ እሱን እናውቀው ዘንድ መስሚያን፣ መመልከቻን እና ልቦናን ሰደረገልን። አዛኙ ጌታችንን እናውቀው ዘንድ እነዚህን እና ሌሎች የማናያቸውን ውለታዎች ለገሰን።

﴿ أَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَى ٱلطَّيۡرِ مُسَخَّرَٰتٖ فِي جَوِّ ٱلسَّمَآءِ مَا يُمۡسِكُهُنَّ إِلَّا ٱللَّهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ٧٩ ﴾

النحل: ٧٩

ወደ በራሪዎች በሰማይ አየር ውስጥ (ለመብረር) የተገሩ ሲኾኑ (ከመውደቅ) አላህ እንጂ ሌላ የማይዘቸው ኾነው አይመለከቱምን?!! በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ሕዝቦች በእርግጥ ተዓምራቶች አሉ። [አል ነሕል 79]

ሳይንስ የመሬት ስበት (gravity) እያለ ቢያወራም ሁሉን ማድረግ የሚችለው ፈጣሪያችን አላህ አሞራዎችን በሰማይ አየር ላይ እንዳይወድቁ፣ እንዲንሳፈፉ አደረጋቸው። ይህንንም ማድረግ የሚችለው ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ የሆነው ከሰባት ሰማያት በላይ ከአርሹ በላይ ያለው ሀያሉ አላህ ነው።

﴿ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ مَهۡدٗا وَسَلَكَ لَكُمۡ فِيهَا سُبُلٗا وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجۡنَا بِهِۦٓ أَزۡوَٰجٗا مِّن نَّبَاتٖ شَتَّىٰ ٥٣ كُلُواْ

وَٱرۡعَوۡاْ أَنۡعَٰمَكُمۡۗ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّأُوْلِي ٱلنُّهَىٰ ٥٤ ﴾ طه: ٥٣ - ٥٤

<u>(እርሱ አላህ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ</u>፣ በእርሷም ውስጥ ለእናንተ መንገድን ያገራላችሁ፣ ውሃንም ከሰማይ ያወረደ ነው (አለ)። በርሱም ከተለያየ በቃይ ዓይነቶችን አወጣንላችሁ። ብሉ እንስሳዎቻችሁንም አግጡ። <u>በዚህ ውስጥ ለአእምሮ ባለቤቶች በእርግጥ ተዓምራት አለበት</u>። [ጣሃ 53-54]

ይህን ሁሉ ያገራልን ከእናት በላይ አዛኝ የሆነው አላህ ሲሆን ሃይልም ጥበብም በአላህ ብቻ ይብቃ።

﴿ ۞ مِنۡهَا خَلَقۡنَٰكُمۡ وَفِيهَا نُعِيدُكُمۡ وَمِنۡهَا نُخۡرِجُكُمۡ تَارَةً أُخۡرَىٰ ٥٥ ﴾ طه: ٥٥

ከእርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ። በእርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን። ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን። [ጣሃ 55]

ከምንም በፊት የነበረው ብቸኛው ፈጣሪያችን አላህ ነው። ከዛም ፍጡራኑን ፈጠረ። በመጨረሻም ፍጡራኖች በተወሰነላቸው ጊዜ ሲሞቱ ሃያሉ ጌታችን ብቻ ይቀራል። አላህ የሰው ልጆችን ከአፈር ፈጠረ። ከዛ የሰው ልጅ ምቶም ወደ አፈር ይመለሳል። በመጨረሻም ከመቃብር ህያው ሆኖ ይቀሰቀሳል። ይህን ብሉ በማድረግ ላይ ቻይ የሆነው አላህ ጥራት ይገባው።

﴿ يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ ٱلۡمَيِّتِ وَيُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتَ مِنَ ٱلۡحَيِّ وَيُحۡيِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَاۚ وَكَذَٰلِكَ تُخۡرَجُونَ ١٩ ﴾ الروم: ١٩

ሕያውን ከሙት ያወጣል። ሙታንም ከሕያው ያወጣል። ምድርንም ከሞተች በኋላ ህያው ያደርጋታል። እንደዚሁም (ከመቃብር) ትወጣላችሁ። [አል ሩም 19]

ይህን ሁሉ ማድረግ የሚችለው ብቸኛው አላህ ነው።

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنۡ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ إِذَآ أَنتُم بَشَرٞ تَنتَشِرُونَ ٢٠ ﴾ الروم: ٢٠

እናንተንም ከዐፈር መፍጠሩ ከዚያም እናንተ ወዲያውኑ የምትበታተኑ ሰዎች መኾናችሁ <u>ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው</u>። [አል ሩም 20]

ከአፈር የፈጠረን፣ ወደ አፈር የሚመልሰን፣ ከዛም ከአፈር ውስጥ (ከቀብራችን) የሚቀሰቅሰን ብቸኛው ፈጣሪ አላህ ነው።

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنۡ خَلَقَ لَكُم مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ أَزۡوَٰجٗا لِّتَسۡكُنُوٓاْ إِلَيۡهَا وَجَعَلَ بَيۡنَكُم مَّوَدَّةٗ وَرَحۡمَةً إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٢١ ﴾ الروم: ٢١

ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) <u>ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው</u>። <u>በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ</u>። [አል ሩም 21]

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ خَلۡقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفُ أَلۡسِنَتِكُمۡ وَأَلۡوَٰنِكُمۡۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّلۡعَٰلِمِينَ ٢٢ ﴾

الروم: ٢٢

<u>ሰማያትንና ምድርንም መፍጠሩ፣ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው</u>። <u>በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ተዓምራቶች አልሉበት</u>። [አል ሩም 22]

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ مَنَامُكُم بِٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱبۡتِغَآؤُكُم مِّن فَضۡلِهِۦٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَسۡمَعُونَ ٢٣ ﴾

الروم: ٢٣

<u>በሌሊትና በቀንም መተኛታችሁ፣ ከችሮታውም መፈለጋችሁ ከምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉበት</u>። [አል ሩም 23]

አላህ በተአምራቶቹ ይታወቃል። ከተአምራቶቹ ውስጥ በሌሊት እና በቀን መተኛታችን፣ ከችሮታውም መፈለጋችን ይገኙበታል።

﴿ وَمِنْ ءَايَـٰتِهِۦ يُرِيكُمُ ٱلْبَرْقَ خَوْفًا وَطَمَعًا وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَيُحْىِۦ بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَآ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَـَٔايَـٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿٢٤﴾ ﴾ الروم: ٢٤

ብልጭታንም (መብረቅንም) ፈሪዎችና ከጃዮች ስትሆኑ ለእናንተ ማሳየቱ፣ ከሰማይም ውሃን ማውረዱ፣ በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። <u>በዚህ ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉበት</u>። [አል ሩም 24]

መሬት በመድረቅ ከሞተች በኋላ፣ ዳመና ዳምኖ መብረቅ ሲነጉድ እንደነግጣለንንም ዝናቡንም በመከጀል እንደሰታለን። ይህን ኡድራጊው ብቸኛ አምላካችን አላህ ነው።

﴿ وَمِنْ ءَايَـٰتِهِۦٓ أَن تَقُومَ ٱلسَّمَآءُ وَٱلْأَرْضُ بِأَمْرِهِۦ ۚ ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمْ دَعْوَةً مِّنَ ٱلْأَرْضِ إِذَآ أَنتُمْ تَخْرُجُونَ ﴿٢٥﴾ ﴾ الروم: ٢٥

ሰማይና ምድርም (ያለምሰሶ) በትዕዛዙ መቆማቸው፣ ከዚያም (መልአኩ ለትንሣኤ) ከምድር ጥሪን በጠራችሁ ጊዜ እናንተ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ <u>ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው</u>። [አል ሩም 25]

የአንድ አምላክ አላህን መኖር ለማወቅ ሰማያትን ምድርን ያለ ድጋፍ እና ያለ ሙሶሶ መፍጠሩ እና ማቆሙ ማስረጃ ናቸው። አስራፊል የተባለው መላእክ በቀንዱ ጡሩንባ ሲነፋ የሰው ልጆች ተቀብረው ከነበሩበት ምድር ሁሉም ይወጣሉ። ልሙጥ በሆነ ሜዳ ላይም ሰዎች ከመጀመሪያቸው እስከ መጨረሻቸው ድረስ እራቁታቸውን፣ ያልተገረዙ እና ባዶ እግራቸውን ሲሆኑ ለአለማቱ ጌታ ለፍርድ ይቀርባሉ።

﴿ وَلَهُۥ مَن فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ كُلٌّ لَّهُۥ قَـٰنِتُونَ ﴿٢٦﴾ ﴾ الروم: ٢٦

<u>በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው።</u> <u>ሁሉም ለእርሱ ታዛዦች ናቸው</u>። [አል ሩም 26]

ብቸኛው ፈጣሪ፣ አምልኮ በጠቅላላ ለእርሱ ብቻ እንደሚገባው በዚህ አንቀፅ ላይ ነገረን።

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِى يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَهُوَ أَهۡوَنُ عَلَيۡهِۚ وَلَهُ ٱلۡمَثَلُ ٱلۡأَعۡلَىٰ فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٢٧ ﴾ الروم: ٢٧

እርሱም ያ መፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ነው። እርሱም (መመለሱ፡- የሞቱትን መቀስቀሱ) በእርሱ ላይ በጣም ገር ነው። ለእርሱም በሰማያትም በምድርም ከፍተኛ ባሕርይ (አንድነትና ለእርሱ ብጤ የሌለው መኾን) አልለው። እርሱም አሸናፊ ጥበበኛ ነው። [አል ሩም 27]

﴿ أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱلۡفُلۡكَ تَجۡرِى فِى ٱلۡبَحۡرِ بِنِعۡمَتِ ٱللَّهِ لِيُرِيَكُم مِّنۡ ءَايَٰتِهِۦٓۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّكُلِّ صَبَّارٖ شَكُورٖ ٣١ ﴾

لقمان: ٣١

<u>ከአስደናቂ ምልክቶቹ ሊያሳያችሁ መርከቦች በአላህ ችሮታ በባህር ውስጥ የሚንሻለሉ መሆናቸውን አታይምን? በዚህ ውስጥ በጣም ታጋሽ አመስጋኝ ለሆኑ ሁሉ ተዓምራቶች አሉበት</u>። [አል ሉቅማን 31]

﴿ أَوَلَمۡ يَهۡدِ لَهُمۡ كَمۡ أَهۡلَكۡنَا مِن قَبۡلِهِم مِّنَ ٱلۡقُرُونِ يَمۡشُونَ فِى مَسَٰكِنِهِمۡۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٍۖ أَفَلَا يَسۡمَعُونَ ٢٦ ﴾

﴾ السجدة: ٢٦

ከከፍለ ዘመናት ሰዎች ብዙዎችን ያጠፋን መሆናችን በመኖሪያዎቻቸው የሚሄዱ ሲሆኑ ለእነርሱ አልተገለፀላቸውምን? <u>በዚህ ውስጥ ምልክቶች አሉት</u>፤ አይሰሙምን? [አል ሰጅዳህ 26]

﴿ أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّا نَسُوقُ ٱلۡمَآءَ إِلَى ٱلۡأَرۡضِ ٱلۡجُرُزِ فَنُخۡرِجُ بِهِۦ زَرۡعٗا تَأۡكُلُ مِنۡهُ أَنۡعَٰمُهُمۡ وَأَنفُسُهُمۡۖ أَفَلَا يُبۡصِرُونَ ٢٧ ﴾

السجدة: ٢٧

<u>እኛ ውሃን ወደ ደረቅ ምድር የምንነዳ</u> <u>እንስሶቻቸውና ነፍሶቻቸው</u> <u>ከእርሱ የሚበሉለትንም አዝመራ በእርሱ የምናወጣ</u> <u>መኾናችንን አያዩምን</u>? <u>አይመለከቱምን</u>?

[አል ሰጅዳህ 27]

﴿ ٱللَّهُ يَتَوَفَّى ٱلۡأَنفُسَ حِينَ مَوۡتِهَا وَٱلَّتِي لَمۡ تَمُتۡ فِي مَنَامِهَاۖ فَيُمۡسِكُ ٱلَّتِي قَضَىٰ عَلَيۡهَا ٱلۡمَوۡتَ وَيُرۡسِلُ ٱلۡأُخۡرَىٰٓ إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمًّىۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٤٢ ﴾ الزمر: ٤٢

አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል። ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)። ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል። ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቅቃታል። <u>በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አልሉበት</u>።

[አል ዙመር 46]

እንቅልፍ የሞት ታናሽ ወንድም ይባላል። እንቅልፋችንን ሰንተኛ ነፍሳችንን አላህ ይይዛታል። ለዛም ነው ሰንተኛ "አላህ ሆይ! ነፍሴን ከያዝካት (በዚሁ እንቅልፌ ከሞትኩ) እዘንላት፣ ከመለስካት ደግሞ ባሪያዎችህን በምትጠብቅበት ጠብቃት።" ሰንል የምንለምነው። ከእንቅልፋችንም ሰንነሳ "ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው፣ ያ በእንቅልፍ ከገደለን በኋላ ህይወታችንን የመለሰልን" ሰንል የምናወድሰው።

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِ ٱلۡجَوَارِ فِي ٱلۡبَحۡرِ كَٱلۡأَعۡلَٰمِ ٣٢ إِن يَشَأۡ يُسۡكِنِ ٱلرِّيحَ فَيَظۡلَلۡنَ رَوَاكِدَ عَلَىٰ ظَهۡرِهِۦٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّكُلِّ صَبَّارٖ شَكُورٍ ٣٣ ﴾ الشورى: ٣٢ - ٣٣

በባሕር ላይ እንደ ጋራዎች ኾነው ተንሻላዮቹም (መርከቦች) ከአስደናቂ ምልክቶቹ ናቸው። ቢሻ ነፋሱን የረጋ ያደርገዋል። በባሕሩም ጀርባ ላይ ረጊዎች ይኾናሉ። <u>በዚህ</u>

ውሰጥ በጣም ታጋሽና አመስጋኝ ለኾነ ሁሉ በእርግጥ ምልክቶች አልሉ። [አል ሹራ 32-33]

﴿ أَوۡ يُوبِقۡهُنَّ بِمَا كَسَبُواْ وَيَعۡفُ عَن كَثِيرٖ ٣٤ ﴾ الشورى: ٣٤

ወይም በሠሩት ኃጢኣት ምክንያት (በማስጠም) ያጠፋቸዋል። ከብዙም ይቅርታ ያደርጋል። [አል ሹራ 34]

﴿ وَيَعۡلَمَ ٱلَّذِينَ يُجَٰدِلُونَ فِيٓ ءَايَٰتِنَا مَا لَهُم مِّن مَّحِيصٖ ٣٥ ﴾ الشورى: ٣٥

(ከእነርሱ ለመበቀል)፤ እነዚያንም በአንቀጾቻችን የሚከራከሩትን ለማወቅ (ያጠፋቸዋል)። ለእነርሱ ምንም መሸሻ የላቸውም። [አል ሹራ 35]

﴿ إِنَّ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ لَأٓيَٰتٖ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ٣ وَفِي خَلۡقِكُمۡ وَمَا يَبُثُّ مِن دَآبَّةٍ ءَايَٰتٞ لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ٤ ﴾ الجاثية: ٣ - ٤

<u>በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምእምናን ሁሉ (ለችሎታው) እርገጠኛ ምልክቶች አልሉ</u>። እናንተንም በመፍጠር ከተንቀሳቃሽም (በምድር ላይ) የሚበትነውን ሁሉ (በመፍጠሩ) <u>ለሚያረጋግጡ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ</u>። [አል ጃሲያህ 3-4]

﴿ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن رِّزۡقٖ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَا وَتَصۡرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ ءَايَٰتٞ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ٥ ﴾

الجاثية: ٥

በሌሊትና በቀን መተካካትም፣ ከሲሳይም (ከዝናም) አላህ ከሰማይ ባወረደው በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው በማድረጉ፣ ነፋሶችንም (በያቅጣጫቸው) በማዘዋወሩ <u>ለሚያውቁ ሕዝቦች ማስረጃዎች አልሉ</u>። [አል ጃሲያህ 5]

﴿ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱللَّهِ نَتۡلُوهَا عَلَيۡكَ بِٱلۡحَقِّۖ فَبِأَيِّ حَدِيثِۭ بَعۡدَ ٱللَّهِ وَءَايَٰتِهِۦ يُؤۡمِنُونَ ٦ ﴾ الجاثية: ٦

<u>እነዚህ ባንተ ላይ በውነት የምናነባቸው ሲኾኑ የአላህ ማስረጃዎች ናቸው</u>። <u>ከአላህና ከማስረጃዎቹም ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ</u>? [አል ጃሲያህ 6]

﴿ وَيۡلٞ لِّكُلِّ أَفَّاكٍ أَثِيمٖ ٧ يَسۡمَعُ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِ ثُمَّ يُصِرُّ مُسۡتَكۡبِرٗا كَأَن لَّمۡ يَسۡمَعۡهَاۖ فَبَشِّرۡهُ بِعَذَابٍ أَلِيمٖ ٨ ﴾

الجاثية: ٧ - ٨

ውሸታም ኀጢአተኛ ለኾነ ሁሉ ወዮለት። (ጥፋት ተገባው)። የአላህን አንቀጾች በእርሱ ላይ የሚነበቡለት ሲኾኑ ይሰማል። ከዚያም የኩራ ሲኾን እንዳልሰማት ኾኖ (በከሕደቱ ላይ) ይዘወትራል። በአሳማሚም ቅጣት አብስረው። [አል ጃሲያህ 7-8]

ኩራት ማለት ሐቅን አለመቀበል እና ሰዎችን በንቀት ማየት ነው። ታላቁ ሐቅ የአላህን አንድነት ነው። ይህ ታላቅ ሐቅ በመለኮታዊ መፀሃፍት ላይ ተቀምጦ፣ በንፁህ አእምሮ የሚረጋገጥ ነገር ሆኖ ሳለ መካድ ከባድ ኩራት ነው። ኩራት (ሀቅን አለመቀበል) ለገሀነም ይረዳል።

﴿ وَإِذَا عَلِمَ مِنۡ ءَايَٰتِنَا شَيۡـٔا ٱتَّخَذَهَا هُزُوًاۚ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عَذَابٞ مُّهِينٞ ٩ ﴾ الجاثية: ٩

ከአንቀጾቻችንም አንዳችን ባወቀ ጊዜ መሳለቂያ አድርጎ ይይዛታል። እነዚያ ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አልላቸው። [አል ጃሲያህ 9]

﴿ مِّن وَرَآئِهِمۡ جَهَنَّمُۖ وَلَا يُغۡنِي عَنۡهُم مَّا كَسَبُواْ شَيۡـٔٗا وَلَا مَا ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوۡلِيَآءَۖ وَلَهُمۡ عَذَابٌ عَظِيمٞ ١٠ ﴾

الجاثية: ١٠

ከፊታቸውም ገሀነም አልለች። የሰበሰቡትም ሀብት ከእነርሱ ላይ ምንንም አይመልስላቸውም። ከአላህ ሌላም ረዳቶች አድርገው የያዙዋቸው (አይጠቅሟቸውም)። ለእነርሱም ታላቅ ቅጣት አልላቸው። [አል ጃሲያህ 10]

﴿ هَٰذَا هُدٗىۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمۡ لَهُمۡ عَذَابٞ مِّن رِّجۡزٍ أَلِيمٌ ١١ ﴾ الجاثية: ١١

ይህ (ቁርአን) መሪ ነው። እነዚያም በጌታቸው አንቀጾች የካዱት ለእነርሱ ከብርቱ ቅጣት የኾነ አሳማሚ ስቃይ አልላቸው። [አል ጃሲያህ 11]

﴿ ۞ ٱللَّهُ ٱلَّذِي سَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡبَحۡرَ لِتَجۡرِيَ ٱلۡفُلۡكُ فِيهِ بِأَمۡرِهِۦ وَلِتَبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِهِۦ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ١٢ ﴾ الجاثية: ١٢

አላህ ያ ባሕርን በውስጡ ታንኳዎች በፈቃዱ እንዲንሻለሉበት ከችሮታውም እንድትፈልጉበት እንድታመሰግኑትም ለእናንተ የገራላችሁ ነው። [አል ጃሲያህ 12]

ዛሬ የአለምን እውነታ ያየ አንዱ ሀገር ከሌሎች ሀገራት ኢቃን፣ ምግብን እና መገልገያዎችን ያስገባል። ሌላኛው ይልካል። ይህ ሁሉ ንግድ የሚጓጓፈው በባህር ላይ መርከቦች ላይ በሚጫኑ በሚሊዬን የሚቆጠሩ ኮንቴነሮች ነው። ይህን ሁሉ ንብረት ተሸክመው በባህር ላይ የሚሄዱ መርከቦች ባህር እና ውቂያኖስን እንዲያቋርጡ ያደረጋቸው አንድ አምላክ አላህ እንጂ ሌላ አይደለም።

﴿ وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ١٣ ﴾ الجاثية: ١٣

ለናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከእርሱ ሲኾን የገራላችሁ ነው። <u>በዚህ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ተዓምራት አልለበት</u>። [አል ጃሲያህ 13]

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِ ٱلَّيۡلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُۚ لَا تَسۡجُدُواْ لِلشَّمۡسِ وَلَا لِلۡقَمَرِ وَٱسۡجُدُواْ لِلَّهِ ٱلَّذِي خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمۡ إِيَّاهُ تَعۡبُدُونَ ٣٧ ﴾ فصلت: ٣٧

ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው። ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ። ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ። እርሱን ብቻ የምትግዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)። [ፉሲለት 37]

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنَّكَ تَرَى ٱلۡأَرۡضَ خَٰشِعَةٗ فَإِذَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡهَا ٱلۡمَآءَ ٱهۡتَزَّتۡ وَرَبَتۡۚ إِنَّ ٱلَّذِيٓ أَحۡيَاهَا لَمُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰٓۚ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ٣٩ ﴾ فصلت: ٣٩

<u>አንተ ምድርን ደረቅ ኾና ማየትህም ከምልክቶቹ ነው</u>። በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ (በቡቃያዎችዋ) ትላወሳለች። ትነፋለችም። <u>ያ ሕያው ያደረጋት ጌታ በእርግጥ ሙታንን ሕያው አድራጊ ነው</u>። <u>እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና</u>። [ፉሲለት 39]

ይሄ ደግሞ ሌላኛው አስደናቂ የአላህ ተአምር ነው።

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ خَلۡقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَثَّ فِيهِمَا مِن دَآبَّةٖۚ وَهُوَ عَلَىٰ جَمۡعِهِمۡ إِذَا يَشَآءُ قَدِيرٞ ٢٩ ﴾

الشورى: ٢٩

ሰማያትንና ምድርንም መፍጠሩ፣ ከተንቀሳቃሽም በሁለቱ ውስጥ የበተነውን (መፍጠሩ) <u>ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው</u>። እርሱም በሚሻ ጊዜ እነርሱን በመሰብሰብ ላይ ቻይ ነው። [አል ሹራ 29]

﴿ قَالَ ٱلۡمَلَأُ ٱلَّذِينَ ٱسۡتَكۡبَرُواْ مِن قَوۡمِهِۦ لِلَّذِينَ ٱسۡتُضۡعِفُواْ لِمَنۡ ءَامَنَ مِنۡهُمۡ أَتَعۡلَمُونَ أَنَّ صَٰلِحٗا مُّرۡسَلٞ مِّن رَّبِّهِۦۚ قَالُوٓاْ إِنَّا بِمَآ أُرۡسِلَ بِهِۦ مُؤۡمِنُونَ ٧٥ ﴾ الأعراف: ٧٥

ከወገኖቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች ለእነዚያ ለተሸነፉት ከነሱ ላመኑት፡- "<u>ሷሊህ ከጌታው መላኩን ታውቃላችሁን?</u>" አሏቸው። "<u>(አዎን)፡- እኛ እርሱ በተላከበት ነገር</u> አማኞች ነን" አሉ። [አል-አዕራፍ 75]

መልክተኞች እና ነብያት የሚላኩት ከብዙኛው ፈጣሪ አላህ ነው። የአላህን መኖር ከምናውቅባቸው መንገዶች ውስጥ ከእኛ በፊት የነበሩት ደጋግ ህዝቦች ሷሊህ የተባሉት የአላህ መልክተኛ በተላኩ ጊዜ "ሷሊህ ከጌታው መላኩን ታውቃላችሁን?" ተብለው በተጠየቁ ጊዜ "አዎን" የሚል መልስ መመለሳቸው ነው።

﴿ قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِنۡ أَخَذَ ٱللَّهُ سَمۡعَكُمۡ وَأَبۡصَٰرَكُمۡ وَخَتَمَ عَلَىٰ قُلُوبِكُم مَّنۡ إِلَٰهٌ غَيۡرُ ٱللَّهِ يَأۡتِيكُم بِهِۗ ٱنظُرۡ كَيۡفَ نُصَرِّفُ ٱلۡأٓيَٰتِ ثُمَّ هُمۡ يَصۡدِفُونَ ٤٦ ﴾ الأنعام: ٤٦

ንገሩኝ አላህ መስሚያችሁንና ማያዎቻችሁን ቢወስድ በልቦቻችሁም ላይ ቢያትም ከአላህ ሌላ እሱን የሚያመጣላችሁ አምላክ ማነው? በላቸው። <u>አንቀጾችን እንዴት እንደምናብራራ ከዚያም እነሱ እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት</u>። [አል-አንዓም 46]

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلنُّجُومَ لِتَهۡتَدُواْ بِهَا فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۗ قَدۡ فَصَّلۡنَا ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٩٧ ﴾

الأنعام: ٩٧

እርሱም ያ ከዋክብትን በየብስና በባሕር ጨለማዎች ውስጥ በእርሷ ትመሩ ዘንድ ለእናንተ ያደረገ ነው። <u>ለሚያውቁ ሕዝቦች አንቀጾችን በእርግጥ ዘረዘርን</u>። [አል-አንዓም 97]

﴿ هُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ ٱلشَّمۡسَ ضِيَآءً وَٱلۡقَمَرَ نُورًا وَقَدَّرَهُۥ مَنَازِلَ لِتَعۡلَمُواْ عَدَدَ ٱلسِّنِينَ وَٱلۡحِسَابَۚ مَا خَلَقَ ٱللَّهُ ذَٰلِكَ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ يُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٥ ﴾ يونس: ٥

እርሱ ያ ፀሐይን አንፀባራቂ ጨረቃንም አብሪ ያደረገ ነው። የዓመታትን ቁጥርና ሒሳብን ታውቁ ዘንድም ለእርሱ መስፈሪያዎችን የለካ ነው። አላህ ይህንን በእውነት እንጂ (በከንቱ) አልፈጠረውም። <u>ለሚያውቁ ሕዝቦች አንቀጾችን ያብራራል</u>። [ዩኑስ 5]

﴿ إِنَّمَا مَثَلُ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا كَمَآءٍ أَنزَلۡنَٰهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَٱخۡتَلَطَ بِهِۦ نَبَاتُ ٱلۡأَرۡضِ مِمَّا يَأۡكُلُ ٱلنَّاسُ وَٱلۡأَنۡعَٰمُ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَخَذَتِ ٱلۡأَرۡضُ زُخۡرُفَهَا وَٱزَّيَّنَتۡ وَظَنَّ أَهۡلُهَآ أَنَّهُمۡ قَٰدِرُونَ عَلَيۡهَآ أَتَىٰهَآ أَمۡرُنَا لَيۡلًا أَوۡ نَهَارٗا فَجَعَلۡنَٰهَا حَصِيدٗا كَأَن لَّمۡ تَغۡنَ بِٱلۡأَمۡسِۚ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٢٤ ﴾ يونس: ٢٤

የቅርቢቱ ሕይወት ምሳሌ ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ፣ በእርሱም ሰውና እንስሳዎች ከሚበሉት የምድር በቃይ ተቀላቅሎበት (እንደ ፋፋ) ምድርም ውበትዋን በያዘችና ባጌጠች ጊዜ ባለቤቶችዋም በርሷ ላይ እነርሱ ቻዮች መኾናቸውን ባሰቡ ጊዜ ትእዛዛችን ሌሊት ወይም ቀን መጥቶባት ትላንት እንዳልነበረች የታጨደች እንዳደረግናት ብጤ ነው። <u>እንደዚሁም ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን</u>። [ዩኑስ 24]

﴿ قُلِ ٱنظُرُواْ مَاذَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَا تُغۡنِي ٱلۡأٓيَٰتُ وَٱلنُّذُرُ عَن قَوۡمٖ لَّا يُؤۡمِنُونَ ١٠١ ﴾ يونس: ١٠١

“በሰማያትና በምድር ያለውን (ተዓምር) ተመልከቱ” በላቸው። <u>ተዓምራቶችና አስፈራሪዎችም ለማያምኑ ሕዝቦች አይጠቅሙም</u>። [ዩኑስ 101]

﴿ وَيُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمُ ٱلۡأٓيَٰتِۚ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ١٨ ﴾ النور: ١٨

<u>ለእናንተም አላህ አንቀጾችን ይገልጽላችኋል</u>። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው። [አል ኑር 18]

﴿ وَلِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٖ مُّحِيطَۢا ١٢٦ ﴾ النساء: ١٢٦

<u>በሰማያት ያለውና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው</u>። <u>አላህም በነገሩ ሁሉ በዕውቀት ከባቢ ነው</u>። [አል-ኒሳዕ 126]

﴿ وَكَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ وَلَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ١٧٤ ﴾ الأعراف: ١٧٤

<u>እንደዚሁም (እንዲያስቡ) እንዲመለሱም አንቀጾችን እናብራራለን</u>። [አል-አዕራፍ 173]

አጠቃላይ መልእክት

እዚህ ምዕራፍ ላይ የመፀሃፉ አዘጋጅ ለመጥቀስ የሞከሩት አጠቃላይ መልዕክት በሚል የነብያትን ተልኮ እና አላማ ምን እንደሆነ ነው። አላህ ብቸኛው ፈጣሪ ሰውንም ሆነ ጋኔንን የፈጠራቸው እሱን በብቸኝነት እንዲያመልኩት ነው። ይህ አምልኮ ምን መምሰል እንዳለበት ደግሞ ከሰው ልጆች የሆኑ፣ ወንዶችን መልከተኛ እና ነብይ አድርጎ ለእያንዳንዱ ህዝብ ይልካል። እነዚህ መልከተኞች አስፈራሪ እና አብሳሪ ሆነው ነው የሚላኩት። የሚያስፈራሩት አላህን በብቸኝነት ሳያመልክ ለቀረ፣ መልከተኞቹን ላልታዘዘ እና ወንጀሎችን ተዳፍሮ ንሰሃ ላልገባ የአላህ ቅጣት እንዳለበት ነው። በአላህ አንድነት አምነው መልካሞችን ለሰሩ፣ መልከተኞቹን ለታዘዙ የአላህ ውዴታ፣ ገነት እንዳላቸው ያበስራሉ። ሁሉም መልከተኞች የመልክታቸው አስኳል መሸከርከሪያው አንድ እና አንድ ብቻ ነው። እሱም አምልኮን በጠቅላላ ለአንድ አላህ ብቻ አድርጉ፣ ከእርሱ ውጭ የሚመለኩትን በጠቅላላ ራቁ የሚል ነው።

﴿ وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَۖ فَمِنۡهُم مَّنۡ هَدَى ٱللَّهُ وَمِنۡهُم مَّنۡ حَقَّتۡ عَلَيۡهِ ٱلضَّلَٰلَةُۚ فَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَٱنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُكَذِّبِينَ ٣٦ ﴾ النحل: ٣٦

በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ "አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ" በማለት <u>መልክተኛን በእርግጥ ልከናል</u>። ከእነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለለ። ከእነሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አልለ። በምድርም ላይ ኺዱ፤ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ። [አል ነሕል 36]

የሰው ልጆች እና ጋኔኖች (ጂኖች) የተፈጠሩት አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው። አላህን እንዴት ብለን ማምለክ እንዳለብን ደግሞ ለኢየንዳንዱ ህዝብ አላህ መልክተኛን ልኮለታል።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱعۡبُدُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ٢١ ﴾ البقرة: ٢١

እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና። [አል-በቀራህ 21]

እኛንም ከእኛ በፊት የነበሩትን የፈጠረው አላህ በብቸኝነት እንድናመልከው "እናንተ የሰው ልጆች ሆይ!" ሲል ያዘናል።

ከኛ በፊት ለነበሩ ህዝቦች የተላለፈ መልእክት

እነዚህ የመፀሃፍቱ ባለቤቶች ይባላሉ። አላህ ልክ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ላይ ቁርዓንን እንዳወረደው፣ በሙሳ (አለይሂ ሰላም) ላይ ተውራትን አውርዷል፣ በኢሳ (አለይሂ ሰላም) ላይ ኢንጂልን በሌሎች ነብያትም ላይ ያወረዳቸው መፀሃፍቶች አሉ። እነዚህ የመፀሃፍት ባለቤቶች ከአላህ የወረዱላቸውን መፃሃፍቶች በመሰረዝ፣ በመደለዝ ብሎም በመጨመር ይታወቃሉ። አላህ ቁርዓን ላይ ኢይሁዳዊያንንም ይሁን ክርስትያኖችን የመጨረሻው መልክተኛ ሙሐመድ ኢብን አብደላህን (አለይሂ ሰላቱ ወሰላም)

እንዲከተሉ፣ ኢሳም ይሁን ኡዘይር ላይ ያለፉትን ድንበር እና የጨመሩትን ባዕድ አምልኮ ይጠነቀቁ ዘንድ ሁሉን አዋቂ የሆነው አላህ በመጨረሻ በላካቸው ነብይ ላይ ባወረደው ቁርዓን ይገሰፁ ዘንድ የሚከተሉትን መልክቶች ያስተላልፍላቸዋል።

﴿ لَقَدۡ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ مَرۡيَمَۖ وَقَالَ ٱلۡمَسِيحُ يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّي

وَرَبَّكُمۡۖ إِنَّهُۥ مَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ ٱلۡجَنَّةَ وَمَأۡوَىٰهُ ٱلنَّارُۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ٧٢ ﴾

المائدة: ٧٢

እነዚያ “አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው” ያሉ በእርግጥ ካዱ። አልመሲህም አለ፡- “የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ።” እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም። [አል-ማኢዳህ 73]

የተባረከችው መርየም የኢምራን ልጅ የሆነው አልመሲሕ (ኢሳ) የመፀሃፍቱ ባለቤቶች ድንበር ቢያልፉበትም አላህን ብቻ ተገዙ ነው ያለው። አላህ ልጅም ሚስትም የለውም። አላህ አልወለደም አልተወለደምም። አልመሲሕንም ይሁን ኡዘይርን የአላህ ልጆች ናቸው ብሎ ለአላህ ብቻ የሚገባውን አምለኮ ለእነርሱም ይሁን ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ ሰው መጨረሻው ምን እንደሆነ ለማወቅ የፈለገ ይህን መልእክት ልብ ይበል “እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖርያው እሳት ናት። ለበደለኞች ምንም ረዳቶች የሏቸውም።”

﴿ وَإِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ءَأَنتَ قُلۡتَ لِلنَّاسِ ٱتَّخِذُونِي وَأُمِّيَ إِلَٰهَيۡنِ مِن دُونِ ٱللَّهِۖ قَالَ سُبۡحَٰنَكَ مَا يَكُونُ لِيٓ أَنۡ

أَقُولَ مَا لَيۡسَ لِي بِحَقٍّۚ إِن كُنتُ قُلۡتُهُۥ فَقَدۡ عَلِمۡتَهُۥۚ تَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِي وَلَآ أَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِكَۚ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ ١١٦ ﴾

المائدة: ١١٦

አላህም፡- “የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን?” በሚለው ጊዜ (አስታውስ)። “ጥራት ይገባህ፤

ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና" ይላል። [አል-ማኢዳህ 116]

ነብዩላህ ኢሳን (አለይሂ ሰላም) እና እናቱን ፍላጎቱ ሳይኖራቸው ሰዎች ቢያመልኳቸውም፣ የፍርዱ ቀን አላህ የሚከተለውን ጥያቄ ነብዩላህ ኢሳን ይጠይቃቸዋል

"የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎች፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ውጭ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን?"

ነብዩላህ ኢሳም እንዲህ ሲል ይመልሳል

"ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቀዋለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና"

ታድያ ይህን እውነታ የመፀሃፍቱ ባለቤቶች ሊያውቁ እና ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ይዘውት በመጡት መልክት እውነተኛ መሆኑን አምነው መተግበር አለባቸው።

ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ይላሉ "የሁዳዊም ይሁን ነሰራኒ (ክርስትያን) የኔን መላክ ሰምቶ ሳያምንብኝ አይሞትም የእሳት ቢሆን እንጂ"። ልብ ሊባል የሚገባው በነብያት ማመን ማለት ይዘውት የመጡትን በአንድ አምላክ አላህ ብቻ እመኑ ከእርሱ ውጭ ያሉትን ራቁ የሚለውን መልክት መቀበል እንጂ ያንን መልክተኛ ማምለክ ማለት አይደለም።

﴿ مَا قُلْتُ لَهُمْ إِلَّا مَآ أَمَرْتَنِي بِهِۦٓ أَنِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمْ ۚ وَكُنتُ عَلَيْهِمْ شَهِيدًا مَّا دُمْتُ فِيهِمْ ۖ فَلَمَّا تَوَفَّيْتَنِي كُنتَ أَنتَ ٱلرَّقِيبَ عَلَيْهِمْ ۚ وَأَنتَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ ﴿١١٧﴾ ﴾ المائدة: ١١٧

"<u>በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል</u> <u>ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ</u> <u>ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም</u>። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጣባቢ ነበርኩ።

በተሞላኸኝም ጊዜ (ባነሳኸኝ ጊዜ) አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነህ።" [አል-ማኢዳህ 117]

ነብዩላህ ኢሳ (ዐለይሂ ሰላም) በውስጣቸው እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ። በውስጣቸውም በነበረ ወቅት ያስተላለፈው መልክት "ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም።"

﴿ إِن تُعَذِّبۡهُمۡ فَإِنَّهُمۡ عِبَادُكَۖ وَإِن تَغۡفِرۡ لَهُمۡ فَإِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ١١٨ ﴾ المائدة: ١١٨

"ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው። ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ" (ይላል)። [አል-ማኢዳህ 118]

ነብዩላህ ኢሳ (ዐለይሂ ሰላም) እንኳን አምልኩኝ ሊሉ ይቅርና ቀጪም መሓሪም አላህ ብቻ መሆኑን ነው ያፀደቁት።

﴿ قَالَ ٱللَّهُ هَٰذَا يَوۡمُ يَنفَعُ ٱلصَّٰدِقِينَ صِدۡقُهُمۡۚ لَهُمۡ جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ١١٩ ﴾ المائدة: ١١٩

አላህ ይላል፡- "ይህ እውነተኞችን እውነታቸው የሚጠቅምበት ቀን ነው። ለእነርሱ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው በውስጣቸው ሁልጊዜ ዘውታሪዎች ሲኾኑ የሚኖሩባቸው ገነቶች አሉዋቸው። አላህ ከእነሱ ወደደ፤ እነርሱም ከእርሱ ወደዱ፤ ይህ ታላቅ ዕድል ነው።" [አል-ማኢዳህ 119]

﴿ لِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا فِيهِنَّۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرُۢ ١٢٠ ﴾ المائدة: ١٢٠

የሰማያትና የምድር በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ንግሥና የአላህ ብቻ ነው። እሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው። [አል-ማኢዳህ 120]

የሰማያትና የምድር በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ንግሥና፣ ባለቤትነት የአላህ ብቻ ነው። ይህን በማድረጉ ላይ ሁሉ ብቸኛ እንደሆነው ብቸኛው ተመላኪ እሱ ብቻ መሆኑንም

አንድ ባርያ ሊያረጋግጥ ይገባዋል። አላህ በመፍጠር፣ በመግደል፣ በመንከባከብ፣ በመስጠት፣ በመንሳት እንዲሁም ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ ነው። ይህንን እውነታ ያወቀ እሱን ብቻ ይገዘል።

﴿ لَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ فَقَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥٓۖ إِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ٥٩ ﴾

﴿ الأعراف: ٥٩

<u>ኑሕን ወደ ወገኖቹ በእርግጥ ላከነው</u>። አላቸውም፦- “ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ለእናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። እኔ በእናንተ ላይ የከባድ ቀንን ቅጣት እፈራላችኋለሁ።” [አል-ኢምራን 59]

ነብዩላህ ኑሕ (አለይሂ ሰላም) ለምድር ህዝቦች የመጀመሪያው መልክተኛ ነው። ኑሕ የተላከበት መልክት እንደሌሎች መልክተኞች ሁሉ እንዲህ የሚል ነበር “ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ለእናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም።” ይህ መልክት በአላህ ብቻ ማመንን ከእርሱ ውጭ በሚመለኩት አማልክት በጠቅላላ መካድን አጠቃሎ የያዘ ነው። ነብዩላህ ኑሕ (አለይሂ ሰላም) የተላከባቸው ህዝቦች ከአላህ ውጭ ድንጋይ ተገዝተው አልነበረም። ይልቁንስ አምስት ደጋግ ሰዎችን አምልከው ነበር። አላህ ዘንድ መላእክትም ይመለክ፣ ነብይም ይመለክ፣ ድንጋይም ይመለክ ሁሉም አምልኮ ውድቅ ናቸው። የአምልኮ አይነት ሁሉ በአላህ ብቻ ላይ የተገደበ ነው። አይደለም ሌላን አካል ተጋርቶበት (ተደርቦበት) ይቅርና የሚሰራው አምልኮ መልክተኞች ባሳዩት መንገድ ተፈፃሚ ካልሆነ ውድቅ ይሆናል።

﴿ ۞ وَإِلَىٰ عَادٍ أَخَاهُمۡ هُودٗاۚ قَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥٓۚ أَفَلَا تَتَّقُونَ ٦٥ ﴾ ﴿ الأعراف: ٦٥

<u>ወደ ዓድም ወንድማቸውን ሁድን ላከን</u>። “ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። (የአላህን ቅጣት) አትፈሩምን?” አላቸው። [አል-አዕራፍ 65]

የአድ ህዝቦች በመባል ለሚታወቁት ደግሞ አላህ ነብየላህ ሁድን ላከላቸው።

﴿ وَإِلَىٰ ثَمُودَ أَخَاهُمْ صَٰلِحًا ۚ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥ ۖ قَدْ جَآءَتْكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ هَٰذِهِۦ نَاقَةُ ٱللَّهِ لَكُمْ ءَايَةً ۖ فَذَرُوهَا تَأْكُلْ فِىٓ أَرْضِ ٱللَّهِ ۖ وَلَا تَمَسُّوهَا بِسُوٓءٍ فَيَأْخُذَكُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٧٣﴾ ﴾

الأعراف: ٧٣

<u>ወደ ሰሙድም ወንድማቸውን ሷሊህን ላከን</u>። አላቸው "ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ (አምልኩ)። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ ምንም አምላክ የላችሁም። (እውነተኛ ለመኾኔ) ከጌታችሁ የኾነች ምልክት በእርግጥ መጥታላችኋለች። ይህች ለእናንተ ተዓምር ስትኾን የአላህ ግመል ናትና ተዋት። በአላህ ምድር ውስጥ ትብላ፤ (ትጠጣም)። በክፉ አትንኳትም። አሳማሚ ቅጣት ይይዛችኋልና።" [አል-አዕራፍ 73]

ለሰሙድ ህዝቦች ደግሞ አላህ ነብየላህ ሷሊህን ላከ።

﴿ وَإِلَىٰ مَدْيَنَ أَخَاهُمْ شُعَيْبًا ۚ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥ ۖ قَدْ جَآءَتْكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ فَأَوْفُوا۟ ٱلْكَيْلَ وَٱلْمِيزَانَ وَلَا تَبْخَسُوا۟ ٱلنَّاسَ أَشْيَآءَهُمْ وَلَا تُفْسِدُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَٰحِهَا ۚ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿٨٥﴾ ﴾ الأعراف: ٨٥

<u>ወደ መድየንም (ምድያን) ወንድማቸውን ሹዓይብን (ላከን)፤ አላቸው</u>፦- "ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም። ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በእርግጥ መጥታላችኋለች። ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ። ሰዎችንም አንዳቾቻቸውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉድሉባቸው። በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። ይህ ምእምናን እንደኾናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው።" [አል-አዕራ 85]

ለመድየን ህዝቦችም አላህ ነብየላህ ሹዓይብን ላከ።

﴿ وَإِلَىٰ عَادٍ أَخَاهُمْ هُودًا ۚ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥ ۖ إِنْ أَنتُمْ إِلَّا مُفْتَرُونَ ﴿٥٠﴾ ﴾ هود: ٥٠

<u>ወደ ዓድም ወንድማቸውን ሁድን (ላክን)</u>። አላቸው፡- “ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። እናንተም ቀጣፊዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም። [ሁድ 50]

﴿ ۞ وَإِلَىٰ ثَمُودَ أَخَاهُمْ صَٰلِحًا ۚ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥ ۖ هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلْأَرْضِ وَٱسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا

فَٱسْتَغْفِرُوهُ ثُمَّ تُوبُوٓا۟ إِلَيْهِ ۚ إِنَّ رَبِّى قَرِيبٌ مُّجِيبٌ ﴿٦١﴾ ﴾ هود: ٦١

ወደ ሰሙዶችም ወንድማቸውን ሷሊህን (ላክን)። “ሕዝቦቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ አምላክ የላችሁም። እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ። በውስጧ እንድታለሚትም አደረጋችሁ። ምሕረቱንም ለምኑት። ከዚህም ወደእርሱ ተመለሱ። ጌታዬ ቅርብ (ለለመነው) ተቀባይ ነውና” አላቸው። [ሁድ 61]

﴿ ۞ وَإِلَىٰ مَدْيَنَ أَخَاهُمْ شُعَيْبًا ۚ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥ ۖ وَلَا تَنقُصُوا۟ ٱلْمِكْيَالَ وَٱلْمِيزَانَ ۚ

إِنِّىٓ أَرَىٰكُم بِخَيْرٍ وَإِنِّىٓ أَخَافُ عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ مُّحِيطٍ ﴿٨٤﴾ ﴾ هود: ٨٤

<u>ወደ መድየንም ወንድማቸውን ሹዐይብን (ላክን)</u>። አላቸው “ሕዝቦቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ለናንተ አምላክ የላችሁም። ስፍርንና ሚዛንንም አታጉድሉ፤ እኔ በጸጋ ላይ ሆናችሁ አያቸኋለሁ። እኔም በእናንተ ላይ የከባቢን ቀን ቅጣት እፈራለሁ። [ሁድ 83]

﴿ وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوْمِهِۦٓ فَقَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥٓ ۖ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ المؤمنون: ٢٣

<u>ኑሕንም ወደ ሕዝቦቹ በእርግጥ ላክነው</u>። ወዲያውም “ሕዝቦቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። አትጠነቀቁምን?!” አላቸው። [ሙዕሚኑን 23]

﴿ وَإِبْرَٰهِيمَ إِذْ قَالَ لِقَوْمِهِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَٱتَّقُوهُ ۖ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿١٦﴾ ﴾ العنكبوت: ١٦

<u>ኢብራሂምንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)</u>። "አላህን ተገዙ ፍሩትም። ይህ የምታውቁ ብትሆኑ ለእናንተ በላጭ ነው። [አል ዓንከቡት 16]

*ይሽው ከላይ ያየናቸው መልክተኞች በጠቅላላ መልክታቸው አንድ ነው። **<u>አላህን በብቸኝነት አምልኩት፣ ተገዙት ከእርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የላችሁም</u>**። ከአላህ ውጭ የሚደረጉ አምልኮዎችን በጠቅላላ ራቁ የሚል ነበርም መልክታቸው።*

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ٥١ ﴾ آل عمران: ٥١

"<u>አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው</u>" (አላቸው)። [አል-ኢምራን 51]

ይህን ንግግር የተናገሩት ዛሬ ከፊሉ አለም ጌታ እያለ በውሸት የሚያመልካቸው እውነተኛው የአላህ መልክተኛ ኢሳ የመርየም ልጅን ነው።

﴿ ذَٰلِكَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَۚ قَوۡلَ ٱلۡحَقِّ ٱلَّذِي فِيهِ يَمۡتَرُونَ ٣٤ ﴾ مريم: ٣٤

"<u>ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው</u>። ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው።" [መርየም 34]

ነብየላህ ኢሳ የመርየም ልጅ እንጂ የአላህ ልጅ አይደለም።

﴿ مَا كَانَ لِلَّهِ أَن يَتَّخِذَ مِن وَلَدٖۖ سُبۡحَٰنَهُۥٓۚ إِذَا قَضَىٰٓ أَمۡرٗا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ٣٥ ﴾ مريم: ٣٥

"<u>ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም</u>። (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ። ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው "ኹን" ነው ወዲያውም ይኾናል።" [መርየም 35]

﴿ وَإِنَّ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ٣٦ ﴾ مريم: ٣٦

"(ዒሳ አለ) "<u>አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት</u>። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።" [መርየም 36]

﴿ وَلَمَّا جَآءَ عِيسَىٰ بِٱلۡبَيِّنَٰتِ قَالَ قَدۡ جِئۡتُكُم بِٱلۡحِكۡمَةِ وَلِأُبَيِّنَ لَكُم بَعۡضَ ٱلَّذِي تَخۡتَلِفُونَ فِيهِۖ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ٦٣ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ٦٤ ﴾ الزخرف: ٦٣ - ٦٤

“ዒሳ በታምራቶች በመጣ ጊዜም አላቸው “በእርግጥ በጥበብ መጣኋችሁ። የዚያንም በርሱ የምትለያዩበትን ከፊሉን ለናንተ ላብራራላችሁ (መጣሁ)። አላህንም ፍሩ። ታዘዙኝም። “<u>አላህ ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት</u>። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።”” [አል ዙኽሩፍ 63-64]

﴿ وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ وَمَلَإِيْهِ فَقَالَ إِنِّي رَسُولُ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٤٦ ﴾ الزخرف: ٤٦

“ሙሳንም በተዓምራቶቻችን ወደ ፈርዖንና ወደ ሹማምንቶቹ በእርግጥ ላከን። “<u>እኔ የዓለማት ጌታ መልክተኛ ነኝ</u>” አላቸውም።” [አል ዙኽሩፍ 46]

የመጨረሻው መልክተኛ (ﷺ)

እዚህ ምዕራፍ ላይ የመጨረሻውን መልክተኛ፣ የነብያት እና የመልክተኞች መደምደሚያ፣ የኢብራሂም ዝርያ፣ የአላህ ወዳጅ፣ የነብያት እና መልክተኞች ሁሉ ወንድም ሙሐመድ የአብደላህ ልጅ (ﷺ) ማን ናቸው? ይዘውት የመጡት መልክት ምንድን ነው? እሳቸው ከመጡ በኋላ ይዘውት የመጡትን መልክት አለመቀበል መጨረሻው ምንድን ነው እና ሌሎችም ጥያቄዎች በአላህ ፍቃድ መልስ ያገኛሉ።

﴿ ٱلَّذِينَ يَتَّبِعُونَ ٱلرَّسُولَ ٱلنَّبِيَّ ٱلۡأُمِّيَّ ٱلَّذِي يَجِدُونَهُۥ مَكۡتُوبًا عِندَهُمۡ فِي ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَٱلۡإِنجِيلِ يَأۡمُرُهُم بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَنۡهَىٰهُمۡ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡخَبَٰٓئِثَ وَيَضَعُ عَنۡهُمۡ إِصۡرَهُمۡ وَٱلۡأَغۡلَٰلَ ٱلَّتِي كَانَتۡ عَلَيۡهِمۡۚ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِهِۦ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَٱتَّبَعُواْ ٱلنُّورَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ مَعَهُۥٓۙ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٥٧ ﴾ الأعراف: ١٥٧

ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ <u>በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን</u> <u>የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ</u> የሚከተሉ ለኾኑት (በእርግጥ እጽፍለታለሁ)። በበጎ ሥራ ያዛቸዋል። ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል። መጥፎ ነገሮችንም በእነርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከእነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በእነርሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል። እነዚያም በእርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከእርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚያድኑ ናቸው። [አል-አዕራፍ 157]

የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ነብይነት በተውራት (ብሉይ ኪዳን) እና በኢንጂል (አዲስ ኪዳን) ላይ የሚገኝ እውነታ ነው።

﴿ قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنِّي رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيۡكُمۡ جَمِيعًا ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۖ فَـَٔامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِ ٱلنَّبِيِّ ٱلۡأُمِّيِّ ٱلَّذِي يُؤۡمِنُ بِٱللَّهِ وَكَلِمَٰتِهِۦ وَٱتَّبِعُوهُ لَعَلَّكُمۡ تَهۡتَدُونَ ١٥٨ ﴾ الأعراف: ١٥٨

“(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- “እናንተ ሰዎች ሆይ! <u>እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ</u>። (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለእርሱ ብቻ የኾነ ነው። እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ያደርጋል። ይገድላልም። በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ። ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት።”” [አል-አዕራፍ 158]

የላካቸው አላህ ለመሆኑ በል ኢየለ መልክት እንዲያስተላልፉ ያዛል። ኑሕን፣ ኢብራሂምን፣ ሙሳን፣ ኢሳን፣ ዩሱፍን፣ ይስሃቅን፣ ያእቁብን፣ አዩብን፣ ሱለይማንን፣ ዳውድን እና ሌሎችንም የላከው አላህ እሳቸውንም መልክት አስይዞ እንደላካቸው እራሱ በቁርዓን ላይ “እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ።” በላቸው በማለት አላህ አዘዛቸው።

﴿ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمًا ﴿٤٠﴾ ﴾

الأحزاب: ٤٠

“ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን <u>የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው</u>። አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።” [አል አሕዛብ 40]

አሁንም እንደምናነበው አላህ ነው የነብዩ ሙሐመድን ነብይነት ያረጋገጠው።

﴿ وَإِذْ قَالَ عِيسَى ٱبْنُ مَرْيَمَ يَٰبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ إِنِّى رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيْكُم مُّصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَىَّ مِنَ ٱلتَّوْرَىٰةِ وَمُبَشِّرًۢا بِرَسُولٍ يَأْتِى مِنۢ بَعْدِى ٱسْمُهُۥٓ أَحْمَدُ ۖ فَلَمَّا جَآءَهُم بِٱلْبَيِّنَٰتِ قَالُوا۟ هَٰذَا سِحْرٌ مُّبِينٌ ﴿٦﴾ ﴾ الصف: ٦

“<u>የመርየም ልጅ ዒሳም፡- “የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላከሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ</u>” ባለ ጊዜ (አስታውስ)። በግልጽ ተዓምራቶች በመጣቸውም ጊዜ “ይህ ግልጽ ድግምት ነው” አሉ።” [አል ሷፋት 6]

ከነብዩ ሙሐመድ (ኣለይሂ ሰላቱ ወሰላም) ሰሞች መካከል አሕመድ፣ ማሂ፣ ሓሺር፣ ሙሐመድ የሚሉት ይገኙበታል። ከላይ በተጠቀሰው አንቀፅ ነብዩላህ ኢሳ (ኣለይሂ ሰላም) ከእርሳቸው በኋላ ስለሚመጣው መልክተኛ አሕመድ ብስራትን ተናግረዋል።

የሕይወት አላማ

የሕይወት አላማችን መብላት፣ መጠጣት፣ መጫወቻ ሳይሆን ለታላቅ አላማ ነው። አላማውም ብቸኛውን ጌታችን አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው። ሰግደታችንን ለእሱ ብቻ ማድረግ፣ ፀሎታችንን ለእሱ ብቻ ማድረግ፣ በእሱ ላይ ብቻ መመካት፤ እሱን ብቻ መፍራት፣ እሱን መከጀል፣ መሃላችንን በእሱ ብቻ መፈፀም፣ ስለታችንን ለእርሱ ብቻ ማድረግ፣ በአጠቃላይ ህይወታችንን እና ሞታችንን ለእሱ ብቻ ማድረግ። አላህን በብቸኝነት ማምለክ እና ከእርሱ ውጭ ባሉት አማልክት በጠቅላላ መካድ፣ በዚህም ላይ

ሃይማኖትን ፍፁም ለእርሱ ብቻ እያጠሩ በፅናት እስከ ሞት መኖር ታላቁ የሕይወት አላማ ነው። አላህ ይህን መንገድ ጠንቅቀው ከሚያውቁት፣ በዛው ላይ ፅንተው ከሚሞቱት ያድርገን። እሱ ለሚወደው ሁሉ እገዛውን ይስጠን ዘንድ እለምነዋለሁ።

﴿ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾ ﴾ الذاريات: ٥٦

“<u>ጋኔንንና ሰውንም በብቸኝነት ሊያመልኩኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም</u>።” [አል ዛሪያት 56]

የተፈጠርነው አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው።

﴿ قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٦٢﴾ ﴾ الأنعام: ١٦٢

““<u>ስግደቴ፣ እርዴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም</u> ለዓለማት ጌታ <u>ለአላህ ነው</u>” በል።” [አል-አንዓም 162]

አምልኮ በጠቅላላ ስግደት፣ እርድ፣ ህይወትም ሆነ ሞት የሚገባው ለአላህ ነው።

﴿ تَنزِيلُ ٱلْكِتَٰبِ مِنَ ٱللَّهِ ٱلْعَزِيزِ ٱلْحَكِيمِ ﴿١﴾ إِنَّآ أَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ بِٱلْحَقِّ فَٱعْبُدِ ٱللَّهَ مُخْلِصًا لَّهُ ٱلدِّينَ ﴿٢﴾ ﴾

الزمر: ١ - ٢

“የመጽሐፉ መወረድ አሸናፊው ጥበበኛው ከኾነው አላህ ነው። እኛ ወደ አንተ መጽሐፉን በእውነት (የተመላ) ሲኾን አወረድነው። <u>አላህንም ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ ያጠራህ ኾነህ ተገዛው</u>።” [አል ዙመር 1-2]

ሃይመኖትን (አምልኮን በጠቅላላ) ለእርሱ ብቻ ያጠራን ሰንሆነ እንድንገዛው ብቻ ነው የታዘዝነው።

﴿ أَلَا لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلْخَالِصُ ۚ وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلْفَىٰٓ إِنَّ ٱللَّهَ يَحْكُمُ

بَيْنَهُمْ فِى مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى مَنْ هُوَ كَٰذِبٌ كَفَّارٌ ﴿٣﴾ ﴾ الزمر: ٣

“ንቁ! ፍጹም ጥሩ የኾነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው። እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች አድርገው የያዙት “ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም” (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም። [አል ዙመር 3]

አለም ላይ ብዙ እምነቶች ይስተዋላሉ። መልከተኞች ሁሉ ይዘዋት ከመጧት አንዲ ኢስላም ውጭ ያሉት በጠቅላላ ከሰረት ውስጥ ናቸው።

ማስረጃዎችን ማቅረብ (ሁጃ)

አላህ ማስረጃን አምጡ እያለ ጥያቄን ይጠይቃል። መንገድ ለሳቱ ሰዎች ማስረጃዎችን ማቅረብ የአላህ አዛኝነቱን የሚጠቁም ነው። ምክንያቱም እሱ ለእኛ የሚፈልግልን ሃቅን አሳይቶን፣ አመስግነነው እኛን ጀነት ማስገባት ነው። አላህ ቁርዓንን አወረደ፣ የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) (ሱና) አስተምሮትም ላይ ከቁርዓን የማይነጠል ማስረጃ ነው። የሰው ልጆች እነዚህን ሁለት ምንጮች የመጀመሪያዎቹ ትውልዶች (ሰሃባዎች) በተረዱት መልክ ቢረዱ ለመቀናት ትልቅ ሰበብ ይሆናቸዋል።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدۡ جَآءَتۡكُم مَّوۡعِظَةٞ مِّن رَّبِّكُمۡ وَشِفَآءٞ لِّمَا فِي ٱلصُّدُورِ وَهُدٗى وَرَحۡمَةٞ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ٥٧ ﴾ يونس: ٥٧

“እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ግሳጼ በደረቶች ውስጥም ላለው (የመጠራጠር በሽታ) መድኃኒት ለምእምናንም ብርሃንና እዝነት በእርግጥ መጣችላችሁ።” [ዩኑስ 57]

መለኮታዊ መፀሃፍት ለሰው ልጆች ማስረጃ ናቸው። የመለኮታዊ መፀሃፎች ሁሉ ጠቅላይ እና የመጨረሻው መልክት አላህ በመጨረሻው ነብይ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ላይ ያወረደው ቁርኣን ነው።

﴿ قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدۡ جَآءَكُمُ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكُمۡۖ فَمَنِ ٱهۡتَدَىٰ فَإِنَّمَا يَهۡتَدِي لِنَفۡسِهِۦۖ وَمَن ضَلَّ فَإِنَّمَا يَضِلُّ عَلَيۡهَاۖ وَمَآ أَنَا۠ عَلَيۡكُم بِوَكِيلٖ ١٠٨ ﴾ يونس: ١٠٨

“እናንተ ሰዎች ሆይ! <u>እውነቱ ከጌታችሁ በእርግጥ መጣላችሁ</u>። (በእርሱ) የተመራም ሰው የሚመራው ለራሱ ነው። የተሳሳተም ሰው የሚሳሳተው (ጉዳቱ) በራሱ ላይ ነው። እኔም በእናንተ ላይ ተጠባቢ አይደለሁም” በላቸው። [ዩኑስ 108]

የመጨረሻው መልእክት ወርዷል። የተቀበለ ጥቅሙ ለራሱ ነው፣ ያስተባበለ እና ያልተቀበለ ደግሞ ጉዳቱ በእራሱ ነው።

﴿ فَذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمُ ٱلۡحَقُّۖ فَمَاذَا بَعۡدَ ٱلۡحَقِّ إِلَّا ٱلضَّلَٰلُۖ فَأَنَّىٰ تُصۡرَفُونَ ٣٢ ﴾ يونس: ٣٢

“እርሱ እውነተኛ ጌታችሁ አላህ ነው። <u>ከእውነትም በኋላ ጥመት እንጂ ሌላ ምን አለ</u>?!! <u>(ከውነት) እንዴት ትዞራላችሁ</u>!!!” [ዩኑስ 32]

﴿ وَقُلِ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكُمۡۖ فَمَن شَآءَ فَلۡيُؤۡمِن وَمَن شَآءَ فَلۡيَكۡفُرۡۚ إِنَّآ أَعۡتَدۡنَا لِلظَّٰلِمِينَ نَارًا أَحَاطَ بِهِمۡ سُرَادِقُهَاۚ وَإِن

يَسۡتَغِيثُواْ يُغَاثُواْ بِمَآءٖ كَٱلۡمُهۡلِ يَشۡوِي ٱلۡوُجُوهَۚ بِئۡسَ ٱلشَّرَابُ وَسَآءَتۡ مُرۡتَفَقٗا ٢٩ ﴾ الكهف: ٢٩

“<u>እውነቱም ከጌታችሁ ነው</u>። የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ” በላቸው። እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል። (ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ። መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች! [አል ከህፍ 29]

ለሚወስዱት ውሳኔ የመወሰን ሃላፊነት

እያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ ለሰራው ተጠያቂ ነው። ሸህ እገሌ፣ አባቴ፣ ጓደኛዬ ይጠየቅልኛል የሚባል አባባል የለም። ሰለዚህ አንተ/ቺ የአላህ ባርያ ሆይ! ለምትወሰደው/ጂው ውሳኔ አንተው/ቺው ሃላፊነት መውሰድን አትዘንጋ/ጊ። የነመን ዘር ፍሬ ያህል ጥሩም የሰራ ያገኘዋል፣ የነመን ዘር ፍሬ ያህል መጥፎም የሰራ ያገኘዋል። እምነትህን ጠንቅቀህ እወቅ/ቂ።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمۡ وَٱخۡشَوۡاْ يَوۡمٗا لَّا يَجۡزِي وَالِدٌ عَن وَلَدِهِۦ وَلَا مَوۡلُودٌ هُوَ جَازٍ عَن وَالِدِهِۦ شَيۡـٔٗاۚ إِنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞۖ

فَلَا تَغُرَّنَّكُمُ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَا وَلَا يَغُرَّنَّكُم بِٱللَّهِ ٱلۡغَرُورُ ٣٣ ﴾ لقمان: ٣٣

“እናንተ ሰዎች ሆይ! ጌታችሁን ፍሩ። <u>ወላጅም ከልጁ (በምንም) የማይጠቅምበትን፤ ተወላጅም እርሱ ወላጁን በምንም ጠቃሚ የማይሆንበትን ቀን ፍሩ</u>። የአላህ ቀጠሮ እውነት ነውና። ቅርቢቱም ሕይወት አትሸንግላችሁ። በአላህም (መታገስ) አታላዩ (ሰይጣን) አያታልላችሁ።” [አል ሉቅማን 33]

ውሳኔ በነፍስ ወከፍ ነው። ወላጅ ለልጁ ሊያዝነት የማይችልበት ቀን አለ። ሁሉም የሚጠቀመውም የሚጎዳውም በነፍስ ወከፍ ነው። ስለዚህ ሰዉ የማንም ይልኝታ ሳይዘው የነብያትን ሁሉ ሃይማኖት እስልምናን ሊቀበል ይገባዋል።

﴿ وَأَنِيبُوٓاْ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ وَأَسۡلِمُواْ لَهُۥ مِن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَكُمُ ٱلۡعَذَابُ ثُمَّ لَا تُنصَرُونَ ٥٤ ﴾ الزمر: ٥٤

“<u>ቅጣቱም ወደእናንተ ከመምጣቱና ከዚያም የማትረዱ ከመኾናችሁ በፊት</u> ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ። [አል ዙመር 54]

﴿ وَٱتَّبِعُوٓاْ أَحۡسَنَ مَآ أُنزِلَ إِلَيۡكُم مِّن رَّبِّكُم مِّن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَكُمُ ٱلۡعَذَابُ بَغۡتَةٗ وَأَنتُمۡ لَا تَشۡعُرُونَ ٥٥

﴾ الزمر: ٥٥

“<u>እናንተ የማታውቁ ስትኾኑም ቅጣቱ በድንገት ሳይመጣባችሁ በፊት</u> ከጌታችሁ ወደናንተ የተወረደውን መልካሙን (መጽሐፍ) ተከተሉ።” [አል ዙመር 55]

﴿ وَإِذۡ تَأَذَّنَ رَبُّكُمۡ لَئِن شَكَرۡتُمۡ لَأَزِيدَنَّكُمۡ وَلَئِن كَفَرۡتُمۡ إِنَّ عَذَابِي لَشَدِيدٞ ٧ ﴾ إبراهيم: ٧

ጌታችሁም “<u>ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ</u> <u>ብትክዱም (እቀጣችኋለሁ) ቅጣቴ በእርግጥ ብርቱ ነውና</u>” በማለት ባስታወቀ ጊዜ (አስታውሱ)። [ኢብራሂም 7]

﴿ ۞ قُلۡ يَتَوَفَّىٰكُم مَّلَكُ ٱلۡمَوۡتِ ٱلَّذِي وُكِّلَ بِكُمۡ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ تُرۡجَعُونَ ١١ ﴾ السجدة: ١١

“<u>በእናንተ የተወከለው መልአከ ሞት ይገድላችኋል</u>። <u>ከዚያም ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ</u>” በላቸው። [አል ሰጅዳህ ፲፩]

﴿ ثُمَّ إِنَّكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ عِندَ رَبِّكُمۡ تَخۡتَصِمُونَ ٣١ ﴾ الزمر: ٣١

“<u>ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን እጌታችሁ ዘንድ ትከራከራላችሁ</u>።” [አል ዙመር 3፩]

﴿ مَّنۡ عَمِلَ صَٰلِحٗا فَلِنَفۡسِهِۦۖ وَمَنۡ أَسَآءَ فَعَلَيۡهَاۖ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ تُرۡجَعُونَ ١٥ ﴾ الجاثية: ١٥

“<u>መልካምን የሠራ ሰው ለነፍሱ ነው</u>። <u>ያከፋም (መጥፎም የሰራ) ሰው በእርሷ ላይ ነው</u>። <u>ከዚያም ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ (ፍርድ ይሰጥባችኋል)</u>።” [አል ጃሲያህ ፲5]

ውጤቱ

የሰው ልጅ ወደዚህ አለም የመጣው በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ኖሮ ለመሞት ብቻ አይደለም። ሙቶ መቀስቀስ ከዛም ለሰሩት ውጤትን ማግኘት አለ። ስለዚህ ውጤት ላለው ሕይወት ምን ሰርቶ መዘጋጀት ብሎም የአምልኮ መስፈርቱ ምንድን ነው? የሚለውን ጠንቅቆ ማወቅ እና ለዛም አለም መዘጋጀት ግድ ይላል።

﴿ وَنُفِخَ فِي ٱلصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ إِلَّا مَن شَآءَ ٱللَّهُۖ ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخۡرَىٰ فَإِذَا هُمۡ قِيَامٞ يَنظُرُونَ ٦٨ ﴾ الزمر: ٦٨

“በቀንዱም ይንነፋል። በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡርና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል። ከዚያም በእርሱ ሌላ (መንነፋት) ይንነፋል። <u>ወዲያውም እነርሱ (የሚሠራባቸውን የሚሰጣቸውን ፍርድ) የሚጠባበቁ ኾነው ቋሚዎች ይኾናሉ</u>።” [አል ዙመር 68]

የመጨረሻው ቀን የሚባለው ይህ ቀን ነው።

﴿ وَأَشۡرَقَتِ ٱلۡأَرۡضُ بِنُورِ رَبِّهَا وَوُضِعَ ٱلۡكِتَٰبُ وَجِاْيٓءَ بِٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَقُضِيَ بَيۡنَهُم بِٱلۡحَقِّ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ ٦٩ وَوُفِّيَتۡ كُلُّ نَفۡسٖ مَّا عَمِلَتۡ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِمَا يَفۡعَلُونَ ٧٠ ﴾ الزمر: ٦٩ - ٧٠

“ምድርም በጌታዋ ብርሃን ታበራለች። <u>መጽሐፉም ይቅቀረባል</u>። ነቢያቱና ምስክሮቹም ይመጣሉ። <u>በመካከላቸውም በእውነት ይፈረዳል</u>። እነርሱም አይበደሉም። <u>ነፍስም ሁሉ የሠራችውን ሥራ ትሞላለች</u>፤ (ትሰፈራለች)። እርሱም የሚሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው።” [አል ዙመር 69-70]

﴿ وَسِيقَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِلَىٰ جَهَنَّمَ زُمَرًاۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءُوهَا فُتِحَتۡ أَبۡوَٰبُهَا وَقَالَ لَهُمۡ خَزَنَتُهَآ أَلَمۡ يَأۡتِكُمۡ رُسُلٞ مِّنكُمۡ يَتۡلُونَ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِ رَبِّكُمۡ وَيُنذِرُونَكُمۡ لِقَآءَ يَوۡمِكُمۡ هَٰذَاۚ قَالُواْ بَلَىٰ وَلَٰكِنۡ حَقَّتۡ كَلِمَةُ ٱلۡعَذَابِ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ ٧١ ﴾ الزمر: ٧١

“እነዚያ የካዱትም የተከፋፈሉ ጭፍሮች ኾነው ወደ ገሀነም ይንዳሉ። በመጧትም ጊዜ ደጃፎቿዋ ይከፈታሉ። ዘበኞቿዋም “ከእናንተ የኾኑ መልክተኞች የጌታችሁን አንቀጾች በናንተ ላይ የሚያነቡላችሁ የዚህንም ቀን መገናኘት የሚያስጠነቅቋችሁ አልመጡዋችሁምን?” ይሏቸዋል። “የለም መጥተውናል፤ ግን የቅጣቲቱ ቃል በከሓዲዎች ላይ ተረጋገጠች” ይላሉ።” [አል ዙመር 71]

﴿ قِيلَ ٱدۡخُلُوٓاْ أَبۡوَٰبَ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ فَبِئۡسَ مَثۡوَى ٱلۡمُتَكَبِّرِينَ ٧٢ ﴾ الزمر: ٧٢

“<u>የገሀነምን ደጃፎች በውስጧ ዘውታሪዎች ስትኾኑ ግቡ</u>። <u>የትዕቢተኞችም መኖሪያ ምን ትከፋ!”ይባላሉ</u>። [አል ዙመር 72]

﴿ وَسِيقَ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوۡاْ رَبَّهُمۡ إِلَى ٱلۡجَنَّةِ زُمَرًاۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءُوهَا وَفُتِحَتۡ أَبۡوَٰبُهَا وَقَالَ لَهُمۡ خَزَنَتُهَا سَلَٰمٌ عَلَيۡكُمۡ طِبۡتُمۡ فَٱدۡخُلُوهَا خَٰلِدِينَ ٧٣ ﴾ الزمر: ٧٣

“እነዚያም ጌታቸውን የፈሩት የተከፋፈሉ ጭፍሮች ኾነው <u>ወደ ገነት ይንነዳሉ</u>። <u>በመጧትም ጊዜ ደጃፎቸዋ የተከፈቱ ሲኾኑ ዘበኞቸዋም ለእነርሱ “ሰላም በናንተ ላይ ይኹን። ተዋባችሁ። <u>ዘውታሪዎች ኾናችሁ ግቧት</u>” ባሏቸው ጊዜ (ይገቧታል)።”
[አል ዙመር 73]

﴿ وَقَالُواْ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِي صَدَقَنَا وَعۡدَهُۥ وَأَوۡرَثَنَا ٱلۡأَرۡضَ نَتَبَوَّأُ مِنَ ٱلۡجَنَّةِ حَيۡثُ نَشَآءُۖ فَنِعۡمَ أَجۡرُ ٱلۡعَٰمِلِينَ ٧٤ ﴾ الزمر: ٧٤

“<u>ምስጋና ለአላህ ለዚያ ተስፋ ቃሉን ለሞላልን። የገነትን ምድር በምንሻው ስፍራ የምንሰፍር ስንኾን ላወረሰን ይገባው</u>” ይላሉም። <u>የሠሪዎችም ምንዳ ምን ያምር</u>!
[አል ዙመር 74]

ስለዚህ (እሺ) አቋምህ የት ላይ ነው?

﴿ قُلۡ إِنَّمَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ فَهَلۡ أَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٨ ﴾ الأنبياء: ١٠٨

“<u>ያ ወደኔ የሚወረደው አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ነው፤ ታዲያ እናንተ ፍጹም ታዛዦች ናችሁን</u>?” <u>በላቸው</u>። [አል-አንዓም 108]

ለዚህ መልክት እጅ እና እግርን በመስጠት ፍፁም ታዛዥ መሆን ግድ ነው።

ምስጋና ሁሉ ለአለማት ጌታ አላህ ይገባው። ይህች በሸይኽ ዶክተር ሷሊህ አል-ሷሊህ (አላህ ይዘንላቸው፣ አላህ ይማራቸው፣ ቀብራቸውን ያስፋላቸው) የተዘጋጀችው ወሳኝ ትምህርት በዚሁ ተጠናቃለች። እኛንም ዝርያዎቻችንንም በነብያት መንገድ ላይ እንዲያደርገን፣ እውቀትን እንዲጨምርልን፣ ፅናትን እንዲሰጠን፣ ወንጀላችን እንዲምርልን፣ መጨረሻችን እንዲያሳምርልን፣ ከቀብር ቅጣት እንዲጠብቀን፣ ሲራጥን እንዲያሻግረን፣ ጀነተል ፊርደው እንዲያስገባን እና የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጎረቤቶች እንዲያደርገን አላህን እለምነዋለሁ። እሱም ሁሉን በማድረግ ላይ ቻይ ነው።

የአላህ ሰላት እና ሰላም በነብያት ሁሉ መደምደሚያ ሙሐመድ (የቃሲም አባት) ላይ፤ በቤተሰባቸው፤ በባልደረቦቻቸው እና ሃቅን በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን።

ጁማዳ አል-አኺራ 1440

የካቲት 2011